# አካባቢ ሳይንስ

## የተማሪዎች መጽሐፍ



**3ኛ ክፍል**

## ይህንን መጽሐፍ በጥንቃቄ በመያዝ ተጠቀምበት/ሚበት




ይህ መጽሐፍ የትምህርት ቤትህ/ሽ ንብረት ነው። ጉዳት እንዳታደርስበት/ሺበት ወይም ጉዳት እንዳይደርስበት ጠብቅ/ጠብቂ።

ይህን መጽሐፍ በጥንቃቄ በመያዝ መከተል ያለበትን መመሪያዎች ተጠቀም/ሚ

1. መጽሐፉን በጋዜጣ፣ በፕሊስቲክ ወይም በተገኘው ወረቀት ሸፍን/ኚ ፡፡
2. መጽሐፉን ሁሌጊዜ ደረቅ እና ንፁህ በሆነ ቦታ አስቀምጥ/ጪ፡፡
3. መጽሐፉን ሁሌጊዜ በንፁህ እጅ ያዝ/ዢ፡፡
4. መጽሐፉን ላይ ምንም አይነት ፅሁፍ አትፃፍ/ፊ፡፡
5. የምትፈልገውን/ጊውን ቦታ በመክፈት ካርድ ወይም ብጣሽ ወረቀት እንደ ምልክት በማስቀመጥ ተጠቀም/ሚ ፡፡
6. አንድም ገፅ ወይም አንድም ስዕል ከውስጡ ለመቅደድ አትሞክር/ሪ፡፡
7. የተቀደደ ገፅ ካለ በማስተሽ ወይም በፕሊስተር አያይዝ/ዢ፡፡
8. በመንገድ ላይም መጽሐፍ በማይጎዳ ሁኔታ ያዝ/ዢ፡፡
9. መጽሐፉን ለሌላ ሰው ስታውስ/ሺ በጥንቃቄ ይሁን፡፡
10. በአዲስ መጽሐፍ ለመጀመሪያ ጊዜ ስትጠቀም/ሚ፣ መጽሐፉን በጀርባ በማስቀመጥ በአንድ ጊዜ ጥቂት ገፆችን ብቻ ገልብጥ/ጪ፡፡ ቀስ ብለህ/ሽ የመጽሐፉን መሃል በእጅህ/ሽ ጫን በል/ይ፡፡ ይህም ዘዴ የመጽሐፉን ሽፋን እንዳይጎዳ ይረዳል፡፡

# የአከባቢ ሳይንስ

## የተማሪዎች መጽሐፍ ሦስተኛ ክፍል


### አዘጋጆች

ዳንኤል እንዳይላሉ ሀይሉ ብሩ

ገቢ ቱሲ ቱፋ ለሚ

ጎሳ ግርማ

### አርታኢዎች

ጋዲሳ በዳዳ ቲጃኒ ሁሴን

ንጉሴ ለማ ዘውዱ ቱሉ

### ገምጋሚዎች

አበራ ከበበዉ ከተማ ፀጋ

ተሰማ ግርማ ጀማል ሙስጠፋ

### ተርጓሚዎች

በቀለ ቀነዓ ደረጀ መኮንን

ቡልቡሉ ዘዉዴ

### ግራፍክስ

ታደሰ ድንቁ

### እሉስቱሬተር

ቡዛዮ ግርማ

© የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ፣ 2014/2021

ይህ መጽሐፍ በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ እና በአሰላ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ትብብር በ2014/2021 ተዘጋጀ፡፡ የዚህ መጽሐፍ የባለቤትነት መብት በህግ የተጠበቀ ነው፡፡ ከኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ፍቃድ ውጪ በሙሉም ሆነ በከፊል ማሳተምም ሆነ አባዝተው ማሰራጨት በህግ ያስጠይቃል፡፡

# መ ውጫ

ይዘት ገፅ


ምዕራፍ 1 .......... 1

ሳይንስን ግልጽ ማድረግ .......... 1

1.1 ምግብና ጤንነት .......... 1

1.2 የምግብ ጥቅም .......... 5

1.3. የግል ንፅህናን መጠበቅ .......... 11

1.4 ቁሶች (ነገሮች) .......... 18

1.5 የብርሃን ጥቅም .......... 25

ምዕራፍ 2 .......... 33

መገኛ .......... 33

2.1 የዞናችን መገኛ .......... 33

2.2 አንጻራዊ መገኛ .......... 36

2.3 ፍጹማዊ መገኛ .......... 37

2፡4 የዞናችን አንጻራዊ መገኛ .......... 40

2.5 የዞናችን ፍፁማዊ መገኛ .......... 41

2.6 የዞናችን ታዋቂ ቦታዎች .......... 43

2.7 የአዋሳኝ ዞኖች ስምና መገኛ .......... 44

ምዕራፍ 3 .......... 50

የተፈጥሮ አከባቢ .......... 50

3.1 የዞናችን አየር ንብረት .......... 50

የአየር ሁኔታና አየር ንብረት ልዩነት ........ 50

3.2 የተፈጥሮ ሀብት ........ 55

የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ሀብት ፍች ........ 55

3.3 የተፈጥሮ ሀብት አስፈላጊነት ........ 60

3.4 ቆሻሻን ማስወገድ ........ 66

3.5 ቆሻሻን ተገቢ ባልሆነ መንገድ ማስወገድ የሚያስከትለው ተፅዕኖ ..... 69

ምዕራፍ 4 ........ 74

ማህበራዊ አከባቢ ........ 74

4.1 የባህል ብዝሃነት ........ 74

4.2 የዞናችን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ........ 80

ምዕራፍ 5 ........ 88

ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች ........ 88

5.1 የመንገድ ላይ ጥንቃቄ ........ 88

5.2 ኤች አይ አቪ /ኤድስ ........ 91

# ምዕራፍ 1

# ሳይንስን ግልጽ ማድረግ

## 1.1 ምግብና ጤንነት

**የግንዛቤ ጥያቄ**

ምግብ ምንድን ነው?

ምግብ ለሰው ልጅ ከሚያስፈልጉት መሰረታዊ ፍላጎቶች ውስጥ አንዱ ነው፡፡ ለጤንነታችን በቂና የተለያዩ የምግብ ዓይነቶች ያስፈልጋሉ፡፡

ለጤንነታችን አትክልትና ፍራፍሬ ምግቦችን መመገብ የተመረጠ ነው፡፡


ጥቅል ጎመን


ቲማቲም


ቀይ ሽንኩርት



አፕል


ነጭ ሽንኩርት


ሙዝ


ማንጎ


ብርቱካን


አቮካዶ

**ሥዕል 1.1 አትክልትና ፍራፍሬ**

ተግባር 1.1

1. ከዚህ በላይ ያሉትን የምግብ ዓይነቶች በማየት አትክልትና ፍራፍሬ በማለት ለይተህ ለክፍል ጓደኞችህ ግለፅ/ጭ፡፡

ጮማና ጨው ያልበዛበት ምግብ መመገብ ለጤንነታችን አስፈላጊ ነው፡፡ እንዲሁም፣ የሰብልና ጥራጥሬ እህሎች ለጤንነታችን አስፈላጊ ናቸው፡፡



ስንዴ



ገብስ



በቆሎ



አተር



ቦሎቄ



በቄላ

ሥዕል 1.2 የሰብልና ጥራጥሬ እህሎች

ስኳር የበዛበት ጣፋጭ ምግቦችን አለመመገብ ለጤንነታችን አስፈላጊ ነው፡፡ ስለዚህ፣ ጣፋጭ ምግቦችን በትንሹ መመገብ ይኖርብናል፡፡



ቅቤ



ጮማ ሥጋ



ኬክ



ቸኮሌት



ክሬም

ሥዕል 1.3 ስኳርና ጮማ የበዛበት ምግቦች

ለሰውነታችን ከሚያስፈልገው መጠን በላይ መመገብ በጤናችን ላይ ጉዳት ሊያስከትል ይችላል፡፡ ይህም፣

- የሰውነት ክብደት ከመጠን በላይ ሊጨምር ይችላል፡፡
- የልብና የደም ቧንቧ ችግር ሊያስከትል ይችላል፡፡
- ለስኳርና ለመሳሰሉት በሽታዎች ሊያጋልጥ ይችላል፡፡

የፍራፍሬ ጭማቂ፣ ውሃና ወተት መጠጣት ለጤናችን ጠቃሚዎች ናቸው፡፡

ተግባር 1.2

1. ለጤናችን ጠቃሚ የሆኑትን ምግቦችና የመጠጥ ዓይነቶችን ምሳሌዎች ዘርዝር/ሪ፡፡
2. በትንሹ መመገብ ያለባቸው ጠፋጭ ምግቦች ምን ምን ናቸው?
3. ስኳር የሚበዛባቸው ምግቦች ምሳሌ በመዘርዘር ግለጽ/ጪ፡፡

## 1.2 የምግብ ጥቅም

የግንዛቤ ጥያቄ

ከምግብ የሚገኙ ጥቅሞች ምን ምን ናቸው?

ምግብ ለሰውነታችን የተለያዩ ጥቅሞችን ይሰጣል፡፡ እነሱም፣

- ጉልበት
- የሰውነት ግንባታ
- ከተለያዩ በሽታዎች ለመከላከል ይጠቅማል፡፡

### የምግብ ምድቦች

የግንዛቤ ጥያቄ

መሰረታዊ የምግብ ምድቦች ምን ምን ናቸው?

መሠረታዊ የምግብ ምድቦች በአራት ይካፈላሉ፡፡ እነርሱም፣ የሰብልና የጥራጥሬ ምድብ፣ የሥጋ ምድብ፣ የወተትና የወተት አስተዋፅኦ ምድብና የአትክልትና ፍራፍሬ ምድብ ናቸው፡፡



የሰብል እህሎች ምድብ



የሥጋ ምድብ



የወተት ምድብ



የአትክልትና ፍራፍሬ ምድብ

ሥዕል 2.4 የምግብ ምድቦች

የምግብ ምድብ ምንጮችና ጥቅሞቻቸውን ቀጥሎ ባለው ሠንጠረዥ 1.1 ውስጥ ተዘርዝሯል፡፡

## ሠንጠረዥ 1.1 የአራቱ የምግብ ምድቦች፣ ምንጮችና ጥቅሞች፡፡

| ተ.ቁ | የምግብ ምድቦች | ምንጭ | ለሰውነታችን የሚሰጡት ጥቅም |
|---|---|---|---|
| 1 | የሰብል እህሎች | ስንዴ፣ ገብስ፣ ሩዝ፣ በቆሎ፣ ማሽላ፣ ኣጃና የመሳሰሉት ናቸው፡፡ | ኃይል ይሰጣሉ |
| 2 | ሥጋ | የከብት ሥጋ፣ የፍየል ሥጋ፣ የበግ ሥጋ፣ የዶሮ ሥጋ፣ ዓሣና የመሳሰሉት ናቸው፡፡ | ሰውነትን ይገነባሉ |
| 3 | ወተት | ወተትና የወተት ውጤቶች እንደ እርጎ፣ ቅቤና አይብ ናቸው፡፡ | ሰውነትን ይገነባሉ |
| 4 | አትክልትና ፍራፍሬ | ፍራፍሬ እንደ ብርቱካን፣ ሙዝ፣ ሎሚ፣ ማንጎ፣ አፕል፣ አቮካዶና የመሳሰሉት ሲሆኑ፤ ከአትክልት እንደ ጎመን፤ ካሮት፤ ሽንኩርትና የመሳሰሉት ናቸው | በሽታን ይከላከላሉ |

ተግባር 1፡3 የሚከተሉት ምግቦች ከየትኛው የምግብ ምድቦች እንደሚመደቡ ግለጽ/ጪ፡፡ ዳቦ፣ ፓስታ፣ እርጎ፣ የዶሮ ሥጋ፣ ቲማቲምና አቮካዶ፡፡

## የምግብ መበከል

የግንዛቤ ጥያቄ

የምግብ መበከል ምንድን ነው?

ለምግብ መበከል ምክንያቶች ምን ምን ናቸው?

በምግብ ውስጥ አለአስፈላጊ ነገሮች ከተገኙ የምግብ መበከል ይባላል፡፡ የተበከለ ምግብ በሽታን ያስከትላል፡፡

ለምግብ መበከል ምክንያቶች በሦስት ይከፈላሉ፡፡ እነሱም፤ ህይወት ያላቸው ነገሮች፤ ኬሚካሎችና አካላዊ ባዕድ ነገሮች ናቸው፡፡

### ህይወት ያላቸው ነገሮች

ህይወት ያላቸው ነገሮች፡- ትላትሎች፤ ባክቴሪያዎች፤ ፈንገሶችና የመሳሰሉት ምግብ ሊበክሉ ይችላሉ፡፡

### ኬሚካሎች

ምግብ ሊበክሉ የሚችሉ ኬሚካሎች፡- ፀረ አረም መድሃንቶች፤ ፀረ-ነፍሳትና ፀረ-አይጥ ናቸው፡

### አካላዊ በዕድ ነገሮች

አካላዊ ባዕድ ነገሮች የሚባሉት እንደ ፕላስቲክ፤ የመስታወት ስብርባሪ፤ የብረት ስብርባሪ፤ የእንጨት ስብርባሪ፤ አፈርና የመሳሰሉት ለምግብ መበከል ምክንያቶች ናቸው፡፡



ፕላስቲክና የመስታወት ስብርባሪ ኬሚካሎች ፀረ አረምና ፀረ ነፍሳት መድሃንቶች

ሥዕል 1.5 ምግብን ሊበክሉ የሚችሉ ነገሮች

## የምግብ መበከል መከላከያ ዘዴዎች

| |
|---|
| የግንዛቤ ጥያቄ |
| የምግብ መበከል መከላከያ ዘዴዎችን ግለጽ/ጪ |

የምግብ ብክለትን ለማከላከል የምግብ ንፅህናን መጠበቅ አስፈላጊ ነው፡፡ የምግብ ብክለትን ለመከላከል የሚከተሉትን ዘዴዎች መጠቀም አስፈላጊ ነው፡፡

1. ንፁህ ውሃ መጠቀም
2. እጅን በደንብ መታጠብ
3. ምግብ የሚዘጋጅበት ዕቃዎችና ቦታ በደንብ ማጽዳት

4. አትክልትና ፍራፍሬን በደንብ ማጠብ

5. ምግብን በደንብ ማብሰል

6. የበሰለ ምግብ ብዙ ግዜ አለማቆየት

7. የበሰለ ምግብ በጥንቃቄ ማስቀመጥ

8. በስሎ የተቀመጠ ምግብ በድጋሚ በደንብ ማሞቅ

9. ነፍሳቶችን፤ አይጥና ሌሎች እንስሳቶችን ከምግብ ማራቅና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

የምግብ ንፅህና አለመጠበቅ በተበከለ ምግብ ለሚመጡ በሽታዎች ያጋልጣል፡፡ በተበከለ ምግብ የሚመጡት በሽታዎችን ለመከላከል ምግብን በንፅህና መጠበቅ፤ በደንብ ማዘጋጀትና ማስቀመጥ ያስፈልጋል፡፡

ተግባር 1.4

ሀ) ምግብን ለማዘጋጀት ምን ዓይነት ውሃ መጠቀም ይኖርብናል?

ለ) እጃችንን የሚንታጠበው መቼ ነው?

ሐ) እጅን መታጠብ ምን ጥቅም አለው?

መ) ምግብን ሊበክሉ የሚችሉት ነፍሳቶች ዘርዝር/ሪ

# 1.3. የግል ንፅህናን መጠበቅ

**የግንዛቤ ጥያቄዎች**

1. የግል ንፅህና ምንድን ነው?
2. የግል ንፅህናን የምንጠብቀው ለምንድነው?

የግል ንፅህናን መጠበቅ ሁል ግዜ መደረግ ያለበት ተግባር ነው፡፡ ይህም፡- ሰውነታችንን መታጠብ፣ ጥርሳችንን መፋቅ፣ በየጊዜው ጥፍራችንን መቆረጥና ማጽዳት፣ ፀጉራችንን መታጠብን ያጠቃልላል፡፡



ሥዕል 1.6 ሰውነትን መታጠብ

ቀን በቀን ኑሮኣችን ውስጥ የተለያዩ ነገሮችን በእጃችን ስንነካካ እንውላለን፡፡ ይህ ደግሞ ለተለያዩ በሽታዎች ሊያጋልጠን ይችላል፡፡ ስለዚህ፤ የእጃችንን ንፅህና በደንብ መጠበቅ አስፈላጊ ነው፡፡

ሽንት ቤት ከተጠቀምን በኋላ ሁል ጊዜ እጃችንን በደንብ በሳሙና መታጠብ አለብን፡፡



ሥዕል 1.7 እጃችንን በውሃና በሳሙና መታጠብ



ሥዕል 1.8 የፀጉር ንፅህና መጠበቅ

የፀጉራችን ንፅህና ካልተጠበቀ እንደ ቅማል ላሉ ነፍሳቶች የመራቢያ ቦታ ሊሆን ይችላል፡፡

የጥርሳችንን ንፅህና መጠበቅ ይጠበቅብናል፡፡ በጥርሳችን ላይ የሚቀር ምግብ ለጥርስ መበስበስ ምክንያት ይሆናል፡፡

ስለዚህ፤ ጥርሳችንን በየቀኑ መፋቅ የአፋችንና የጥርሳችንን ንፅህና ለመጠበቅ ያገለግላል፡፡



ሥዕል 1.9 የጥርስ ንፅህናን መጠበቅ

የልብሳችን ንፅህና በደንብ መጠበቅ ይኖርብናል፡፡ ልብሳችንን በየጊዜው በውሃና በሳሙና በደንብ ማጠብ አስፈላጊ ነው፡፡ የልብስ ንፅህና ካልተጠበቀ እንደ ቁንጫና ቅማል ያሉ ነፍሳቶች መራቢያ ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡



ሥዕል 1.10 የልብስ ንፅህና መጠበቅ

## ንፅህናችንን ባለመጠበቅ በሌሎች ሰዎች ላይ የሚያመጠው ተፅዕኖ

**የግንዛቤ ጥያቄ**

ንፅህናችንን ባለመጠበቅ በሌሎች ሰዎች ላይ ሊያመጣ የሚችለው ተፅዕኖ ምንድን ነው?

የግል ንፅህናን በደንብ መጠበቅ ከተለያዩ በሽታዎች ለመከላከል ይረዳል፡፡ የግል ንጽህና መጠበቅ በማህበራዊ ኑሮ ውስጥ ትልቅ ጥቅም ይኖረዋል፡፡ የግል ንጽህናን ካለመጠበቅ የተነሣ መጥፎ ጠረን ሊፈጠር ይችላል፡፡ ይህ ደግሞ በሌሎች ሰዎች ላይ ተጽዕኖ ሊያመጣ ይችላል፡፡ እንዲሁም፤ የግል ንጽህናን አለመጠበቅ ለተለያዩ ተላላፊ በሽታዎች ሊያጋልጠን ይችላል፡፡

## በንጽህና ጉድለት የሚመጡ በሽታዎች

**የግንዛቤ ጥያቄ**

በንጽህና ጉድለት ምክንያት የሚከሰቱ በሽታዎች ምን ምን ናቸው?

የሚከተሉት በሽታዎች በንፅህና ጉድለት ምክንያት ሊከሰቱ ይችላሉ፡፡ እነሱም፡-

- ተቅማጥ
- ጉንፋን
- ኮሮና
- የጥርስ መበስበስ
- የሰውነት ሙቀት መጨመር
- ፎሮፎር ፤ቋቁቻና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

## ጤናኛና ጤናኛ ያልሆኑ ሰዎችን ማወዳደር

| |
|---|
| የግንዛቤ ጥያቄ<br>ጤናኛና ጤናኛ ያልሆኑ ሰዎች መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው? በማወዳደር ግለጽ/ጪ፡፡ |

ጤንነት፤ በሰውነት፣ በጭንቅላትና በማህበራዊ ኑሮ ሙሉ ሆኖ መገኘት ነው፡፡ ጤናማ የሆነ ሰው የሰውነት አካሉ በትክክል ይሰራል፡፡ ጤናማ የሆኑ ሰዎች በማህበራዊ ኑሮ ውስጥ መሳተፍ ይችላሉ፡፡ በሌላ በኩል ጤናማ ያልሆኑ ሰዎች የሰውነታቸው አካል በትክክል መስራት አይችልም፡፡ በማህበራዊ ኑሮ ውስጥም በትክክል መሳተፍ አይችሉም፡፡

ጤናማ የሆኑና ጤናማ ያልሆኑ ሰዎች መካከል ብዙ ልዩነቶች ይኖራል፡፡

ከዚህ በታች ያለው ሠንጠረዥ 2. 2 ውስጥ ጤናማ በሆኑና ጤናማ ባልሆኑ ሰዎች መካከል ያለውን ልዩነት ይገልፃል፡፡

**ሠንጠረዥ 1.2 ጤናማ በሆኑና ጤናማ ባልሆኑ ሰዎች መካከል ያለው ልዩነት፡፡**

| ጤናማ የሆኑ ሰዎች | ጤናማ ያልሆኑ ሰዎች |
|---|---|
| በሰውነት፣ በጭንቅላትና በማህበራዊ ኑሮ ሙሉ ናቸው፡፡ | በሰውነት፣ በጭንቅላትና በማህበራዊ ውስጥ ችግር ሊኖራቸው ይችላል፡፡ |
| የሰውነት ክፍሎች ስራቸውን በትክክል መስራት ይችላሉ፡፡ | የሰውነት ክፍሎች በትክክል አይሰሩም፡፡ |
| በማህበረሰብ ውስጥ በደስታ ስሜት ይኖራሉ፡፡ | የደስታ ስሜት አይሰማቸውም፡፡ |
| መስራት የሚፈልጉትን ስራ በጥሩ ሁኔታ መስራት ይችላሉ፡፡ | መስራት የሚፈልጉትን ስራ በጥሩ ሁኔታ እንዲሁም በጭራሽ መስራት አይችሉም፡፡ |
| ስራ የመስራት ኃይልና ፍላጎት አላቸው፡፡ | ስራ የመስራት ኃይልና ፍላጎት የላቸውም፡፡ |

## ለታመሙ ሰዎች የሚደረግ እንክብካቤና ትኩረት

**የግንዛቤ ጥያቄ**

ለታመሙ ሰዎች የሚደረግላቸው እንክብካቤ ምን ምን ናቸው?

ለታመሙ ሰዎች ትኩረትና እንክብካቤ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ ለታመሙ ሰዎች የሚከተሉት እንክብካቤዎች ሊደረግላቸው ይገባል፡፡

- ፍቅር ማሳየት፡፡
- ንጹህ ቦታ፣ በቂ አየርና ብርሃን እንዲያገኙ ማድረግ፡፡
- የተመጣጠነ ምግብ እንዲያገኙ ማድረግ፡፡
- የሰውነታቸውን ንጽህና በደንብ መጠበቅ፡፡
- የአቀማመጣቸውን ሁኔታ ምቹ ማድረግ፡፡
- በሀኪም የታዘዘላቸውን መድሃኒት በትክክል እንዲወስዱ ማድረግ፡፡
- ወደ ህክምና በመውሰድ አስፈላጊውን ህክምናና ምክር እንዲያገኙ ማድረግ፡፡

ተግባር 1.5

1. የግል ንጽህናን መጠበቅ ምን ምን በውስጡ ያካትታል?
2. የፀጉራችን ንጽህና ካልተጠበቀ የሚያስከትለው ችግር ምንድን ነው?
3. በግል ንጽህና ጉድለት ሊከሰቱ የሚችሉት በሽታዎች ምን ምን ናቸው?
4. ጤናማ በሆኑና ጤናማ ባልሆኑ ሰዎች መካከል ያለውን ልዩነት ግለጽ/ጪ?
5. ለታመሙ ሰዎች የሚደረግላቸውን እንክብካቤዎች ግለጽ/ጪ?

# 1.4 ቁሶች (ነገሮች)

**የግንዛቤ ጥያቄዎች**

1. በአካባቢያችሁ የሚገኙ ነገሮች ምን ምን ናቸው?
2. በመማሪያ ክፍላችሁ ውስጥ ያሉትን ነገሮች በጥቂቱ ዘርዝር/ሪ፡፡

በአካባቢያችን የሚገኙት ነገሮች ውሃ፣ ዕፅዋት፣ አፈር፣ ድንጋይ አየርና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

በመማሪያ ክፍል ውስጥ ሊገኙ የሚችሉት ነገሮች በጥቂቱ፣ ብዕር ፣ደብተር፣ መቀመጫ፣ ጥቁር ሰሌዳና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

**የግንዛቤ ጥያቄ**

በአካባቢያችሁ የሚገኙት ነገሮች በስንት ሁነት ይገኛሉ?

ነገሮች ወይም ቁሶች በሶስት ሁነት ይከፈላሉ፡፡ እነርሱም፤ ጠጣር፣ ፈሳሽና ጋዝ ናቸው፡፡

**ተግባር 2.6**

እንደ ውሃ፣ አየር፣ አፈር፣ ዘይት፣ ድንጋይ፣ የውሀ እንፋሎት በሁነታቸው በመለየት በወረቀት ላይ ጻፍ/ፊ?


| ጠጣር | ፈሳሽ | ጋዝ |
|---|---|---|
| | | |
| | | |

## የጠጣር፣ ፈሳሽና ጋዝ ፍቺ

የግንዛቤ ጥያቄ

ጠጣር ምንድን ነው?

ጠጣር ነገሮች የራሳቸው የሆነ ይዘትና ቅርጽ አላቸው፡፡ ለምሳሌ፡- ድንጋይ፣ እንጨት፣ የምግብ ጨው ፣ መቀመጫ፣ መፅሐፍ፣ እርሳስ፣ ጥቁር ሰሌዳና የመሳሰሉት ናቸው፡፡



እርሳስ



መፅሐፍ



እንጨት



ድንጋይ

ሥዕል 1፡11 ጠጣር ነገሮች

የግንዛቤ ጥያቄ

ፈሳሽ ምንድን ነው?

ፈሳሽ የራሳቸው የሆነ ይዘትና ቅርጽ የላቸውም፡፡ ፈሳሽ እንደ ጠጣሮች ሁነት ናቸው፡፡ እንዲሁም፡- ቦታ ይይዛሉ፡፡ ይሁን እንጂ፣ የራሳቸው የሆነ ይዘት ስላሌላቸው የተጨመረበትን

እቃ ቅርጽ ይይዛል፡፡ ለምሳሌ፡- ውሃ፣ ወተት፣ ዘይት፣ ጁስና የመሳሰሉት ቦታ የሚይዙ ቢሆኑም የራሳቸው የሆነ ቅርጽ የላቸውም፡፡


ጭማቂ


ውሃ


ወተት

ሥዕል 1.12 ፈሳሽ ነገሮች

ጋዝ

| |
|---|
| የግንዛቤ ጥያቄ<br>ጋዝ ምንድን ነው? |

ጋስ የራሳቸው የሆነ ይዘትና ቅርጽ የሌላቸው ሁነት ናቸው፡፡ ለምሣሌ፤ የውሃ እንፋሎት፣ ኦክስጅን፤ ሀይዲሮጂንና የመሳሰሉት ናቸው፡፡


የውሃ እፋሎት


በአየር የተሞላ ፊኛ


በሲሊንደር ውስጥ ያለው ኦክስጅን

ሥዕል 1.13 ጋዞች

## ተግባር 1.7

የሚከተሉትን ነገሮች በሁኔታቸዉ በመመደብ ለዩ?


ወተት


መኪና


ድንጋይ


ውሃ


ከፋብሪካ የምወጣ ጭስ


ቡና


የውሃ እንፋሎት


የመኪና ጭስ


ወንበር

ውሃ የፋብሪካ ጪስ የ


ንፋስ


ላፕቶፕ


ፋስ

ንፋስ ላፕ ቶፕ መዶሻ

## የጠጣር፣ ፈሳሽና ጋዞች ባህሪያት

### አንድ ነገር ከሌላው የሚለይበት የራሱ የሆነ ባህሪይ አለው፡፡

እያንዳንዱ ጠጣሮች፣ ፈሳሾችና ጋሶች የሚታወቁበት ባህሪይ አላቸው፡፡ እነሱም፡- ቀለም፣ ሽታ፣ ቅርፅና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

ለምሣሌ፡- ጠጣሮች የራሳቸው የሆነ ቅርፅ ሲኖራቸው ፈሳሾችና ጋዞች ደግሞ የራሳቸው የሆነ ቅርፅ የላቸውም፡፡

እነዚህ ባህርያት የነገሮችን ባህሪ ለመለየት ያገለግላሉ፡፡

ተግባር 1.8

**የጠጣርን ባህሪ ለመለየት ጠመኔና ጥቁር ድንጋይን በመውሰድ የሚከተሉትን ተግባራት ሥራ/ሪ፡፡**

1. በቀለማቸው ዓይነት ላይ በመመርኮዝ አካላዊ ባህርያቸውን ለይ፡፡
2. ከሁለቱ ነገሮች ጥንካሬ ያለው የቱ ነው?

**የጋሶችን ባህሪ ለማጥናት የሚከተሉትን ተግባራት ሥራ/ሪ::**

3. ባዶ ብርጭቆ ወደ ታች በማዘቅዘቅ ወደ ውሃ ውስጥ በመግፋት ምን እንደሚሆን ተመልከት/ቺ፡፡
4. ውሃ ወደ ብርጭቆ ውስጥ ለምን አልገባም ብለህ /ሽ ታስባለህ/ሺ፡፡

## የጠጣር ፈሳሽና ጋስ ልዩነቶች

**የግንዛቤ ጥያቄ**

በጠጣር፣ በፈሳሽና በጋስ መካከል ባለው ልዩነት ላይ በቡድን በመወያየት በክፍል ውስጥ ግለፅ/ጪ፡፡

የጠጣር፣ ፈሳሽና ጋስ ልዩነቶችን በቅንጣቶቹ መጠጋጋትና መራራቅ ሊገለጹ ይችላሉ፡፡ ጠጣሮች፣ ፈሳሾችና ጋሶች የሚለዩበት በህሪያቶች አላቸው፡፡ እነሱም፤- የቅርፅ፣ መታመቅ፣ እፍግታ፣ የይዘትና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

ሠንጠረዥ 1.3 የጠጣሮች፣ የፈሳሾችና የጋሶች ልዩነት

| ጠጣር | ፈሳሽ | ጋስ |
|---|---|---|
| የራሳቸው የሆነ ቅርጽ አላቸው፡፡ | የራሳቸው የሆነ ቅርጽ የላቸውም፡፡ | የራሳቸው የሆነ ቅርጽ የላቸውም፡፡ |
| አይታመቅም፡፤ | አይታመቅም፡፡ | ይታመቃል፡፤ |
| ትልቅ እፍግታ አላቸው፡፡ | ከጠጣር ያነሰ እፍግታ አላቸው፡፡ | ትንሽ እፍግታ አላቸው |
| በቀላሉ አይበታተንም | በቀላሉ ይበታተናሉ | በቀላሉ ይበታተናሉ |

## የጠጣር፣ ፈሳሽና ጋስ የሁነት ለውጥ

**የግንዛቤ ጥያቄ**

**የሁነቶች ለውጥ ምንድን ነው?**

አንድ ነገር በተለያየ ሁኔታ ውስጥ የተለየው ሁነቶች ሊኖሩት ይችላል፡፡ የነገሮች በተለያየ ሁነቶች መገኘት የሁነቶች ለውጥ ይባላል፡፡ ይህ የሁነት መቀየር የአካላዊ የሁነት ለውጥ ምሣሌ ነው፡፡

ለምሣሌ፡- ውሃ ከበረዶ ወደ ውሃ /ፈሳሽ፣ ከፈሳሽ ወደ እንፋሎት/ጋስ ይቀየራል፡፡







ጠጣር በረዶ　　ውሃ ፈሳሽ　　የውሃ እንፋሎት

ሥዕል 1.14 አካላዊ የሁነት መቀየር (ጠጣር፣ ፈሳሽና ጋስ)

ተግባር 1፡9

ውሃን በማንቆርቆሪያ ውስጥ በመጨመር እሳት ላይ በመጣድ አስተውሉ፡፡ ውሃ ወደ ምን ይለወጣል? ይህ ለውጥ ምንን ያሳያል?





በማንቆርቆሪያ ውስጥ ያለ ውሃ

እየፈላ ያለ ውሃ

## 1.5 የብርሃን ጥቅም


የግንዛቤ ጥያቄ

የብርሃን ጥቅም ምንድን ነው?

ስለብርሃንና የብርሃን ምንጮች በሁለተኛ ክፍል የአካባቢ ሳይንስ ውስጥ ተምረሃል/ሻል ብርሃን ብዙ ጥቅሞች አሉት፡፡ ከጥቅሞቹ ውስጥ ጥቂቶቹ፡-


1. ነገሮችን ለማየት

የብርሃን ጨረር ከምንጩ በመነሳት በነገሮች ላይ በመረፍ አንጸባርቆ ወደ አይናችን ውስጥ በመግባት ነገሮችን እንድናይ ያደርጋል፡፡




ሥዕል 1፡15 ነገሮችን ማየት


2. አረንጓዴ ዕፅዋቶች ምግባቸውን ለማዘጋጀትና ለማደግ የፀሐይ ብርሃንን ይጠቀማሉ፡፡




ሥዕል 1፡16 እጸዋቶች ብርሃንን ሲጠቀሙ

### 3. ለሀይል ምንጭ

የፀሐይ ብርሃን ጨረር በብረት ሶላር ፕሌት ላይ በማረፍ ኤሌክትሮኖች እንዲመነጩ ያደርጋል፡፡ እነዚህ ኤሌክትሮኖች በመንቀሳቀስ የኤሌክትሪክ ሀይል እንድናገኝ ያደርጋል፡፡




ሥዕል 1፡17 ከፀሐይ ብርሃን የሚገኝ የኤሌክትሪክ ሀይል

4. ሳተላይቶች በህዋ ውስጥ እንድቀሳቀሱ ከፀሐይ ሀይል ያገኛሉ፡፡ በአጠቃላይ ብርሃን ህይወት ላላቸው ነገሮች ሁሉ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

- ምግብ ለኑሮ መሰረታዊ ከሆኑት ነገሮች ውስጥ አንዱ ነው፡፡
- ምግብ ለሀይል ምንጭ፣ ለሰውነት ግንባታ፣ በሽታን ለመከላከልና ለመሳሰሉት ይጠቅማል፡፡
- ዋና ዋና የምግብ ምድቦች የሰብልና ጥራጥሬ፣ ሥጋ፣ ወተት፣ አትክልትና ፍራፍሬ ናቸው፡፡
- ምግብ ሕይወት ባላቸው፣ በኬሚካሎችና በፊዚካላዊ ባዕድ ነገሮች ልበከል ይችላል፡፡
- ነገሮች (ቁሶች) በሁነታው ላይ በመመስረት ጠጣር፣ ፈሳሽና ጋስ በመባል ይመደባሉ፡፡

# የምዕራፍ 1 መልመጃዎች

## I. ትክክል የሆነዉ እውነትስህተት የሆነዉን ደግሞ ሀሰት በማለት መልስ/ሺ

1. ምግብ ለሰው ልጅ ከሚያስፈልጉት መሠረታዊ ፍላጎቶች ውስጥ አንዱ ነው፡፡
2. ጣፋጭ ምግቦችን በብዛት መመገብ ለጤንነታችን አስፈላጊ ነው፡፡
3. ጨው የበዛበት ምግቦችና መጠጦችን መጠቀም በጤንነታችን ላይ ችግር ሊያመጣ ይችላል፡፡
4. የሰውነታችን ክብደት ከመጠን በላይ መጨመር የጤንነት መታወክ ምልክት ነው፡፡
5. ብስኩትና ከረሜላን በብዛት መብላት ጤናችንን ሊያውክ ይችላል፡፡
6. መሠረታዊ የምግብ ምድቦች በሁለት ይከፈላሉ፡፡
7. ስንዴ፤ገብስ ፤ሩዝና በቆሎ የሰብል እህሎች ምሳሌ ናቸው፡፡
8. የከብት፤ የፍየል፤ የበግና የአሣ ስጋ ለሰውነት እድገት አስፈላግዎች ናቸው፡፡
9. እንደ ጎመን ካሮትና ሽንኩርት ያሉት ዕፅዋቶች የፍራፍሬ ምድቦች ናቸው፡፡

10. ምግብን በደንብ ማብሰል የምግብ መበከልን ለመከላከል ይረዳል፡፡

11. ነገሮች በሶስት ሁነቶች ይገኛሉ፡፡

12. በጠጣር ሁነት የሚገኙት ነገሮች የራሳቸው ይዘትና ቅርጽ ይኖራቸዋል፡፡

13. ብርሃን ለእንሰሳቶች አስፈላጊ አይደለም፡፡

14. ብርሃን ለዕፅዋቶች እድገት እንጂ ምግባቸውን ለማዘጋጀት አያስፈልጋቸውም፡

## II. በ ለ ሥር ያሉትን በ ሀ ሥር ካሉት ጋር አዛምድ/ጂ

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. ለሰውነት እድገት ይውላል | ሀ. ፍራፍሬዎች |
| 2. ሰውነትን ከበሽታ ይከላከላል | ለ. ሥጋና ወተት |
| 3. ምግብን የሚበክሉ እንስሳቶች | ሐ. ፀረ ነፍሳት |
| 4. ምግብን በደንብ ማስቀመጥ | መ. ባክቴሪያ |
| 5. ምግብን የሚበክሉ ኬሚካሎች | ሠ. የምግብ ንጽህና |

## III. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል ምረጥ/ጪ፡፡

1. ከሚከተሉት ውስጥ የምግብ ጥቅም የሚገልጸው የቱ ነው?

ሀ. ጉልበት ይሰጣል

ለ. በሽታን ይከላከላል

ሐ. ለሰውነት ግንባታና እድገት

መ. ሁሉም መልስ ናቸው

2. ከሚከተሉት የምግብ ምድቦች ውስጥ ለሰውነት ሙቀትና ጉልበት የሚሰጥ የቱ ነው?

ሀ. የሰብል አህሎች

ለ. አትክልትና ፍራፍሬ

ሐ. ሥጋ

መ. ወተትና የወተት ውጤቶች

3. ከሚከተሉት ዕፅዋቶች ውስጥ የፍራፍሬ ምድብ ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. ብርቱካን ሐ. ቲማቲም

ለ. ሙዝ መ. ማንጎ

4. ለምግብ መበከል ምክንያት የሆነው የቱ ነው

ሀ. ፊዚካላዊ ባዕድ ነገሮች ሐ. ኬሚካሎች

ለ. ህይወት ያላቸው ነገሮች መ. ሁሉም መልስ ናቸው

5. ለምግብ መበከል መከላከያ ዘዴ ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ. ምግብን ለረጅም ጊዜ ማቆየት

ለ. አትክልቶችን በደንብ ማጠብ

ሐ. እጅን በደንብ መታጠብ

መ. ምግብን በደንብ ማብሰል

6. ከሚከተሉት ነገሮች ውስጥ በሁነቶች ልዩ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. በረዶ　　ሐ. መቀመጫ

ለ. ወተት　　መ. ድንጋይ

7. ከሚከተሉት ነገሮች ውስጥ የጋስ ሁነት ያለው የትኛው ነው?

ሀ. አየር　　ሐ. ዘይት

ለ. ውሃ　　መ. ጨው

8. ከሚከተሉት ውስጥ የጠጣር ባህርይ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. በቀላሉ ይታመቀል　　ሐ. በቀላሉ ይበታተናል

ለ. ትንሽ እፍግታ አለው　　መ. የራሱ ቅርጽ አለው

9. በፈሳሽ ላይ ሙቀት ሲጨመር ወደ ምን ይቀየራል?

ሀ. ወደ ጋስ　　ሐ. አይቀየርም

ለ. ወደ ጠጣር　　መ. መልስ የለውም

10. በረዶ ከፍሪጅ ውስጥ ሲወጣ ወዴት ይቀየራል

ሀ. ወደ ውሃ እንፋሎት　　ሐ. ወደ ጠጣር

ለ. ወደ ፈሳሽ ውሃ　　መ. አይቀየርም

# ምዕራፍ 2

## 2. መገኛ

**የግንዛቤ ጥያቄ**

መገኛ ማለት ምን ማለት ነዉ?

መገኛ ማለት አንድ ቦታ ወይም ሀገር የት እንደሚገኝ የሚገልጽ ነው፡፡ መገኛ በሁለት መንገድ ይገለፃል፡፡ እነርሱም አንጻራዊ እና ፍጹማዊ መገኛ ይባላሉ፡፡ የተለያዩ ቦታዎች መገኛ አቅጣጫዎችን በመጠቀም መግለጽ እንችላለን፡፡ አራት ዋና ዋና አቅጣጫዎች አሉ፡፡ እነሱም ሰሜን፣ ደቡብ፣ ምሥራቅና ምዕራብ ናቸው፡፡

### 2.1 የዞናችን መገኛ

**የግንዛቤ ጥያቄ**

ዞን ማለት ምን ማለት ነዉ?

ዞን ማለት የተለያዩ ወረዳዎችን በውስጡ የያዘ ነዉ፡፡ በዚህ መልኩ ኦሮሚያ 21 ዞኖችና ከዞኖች ጋር እኩል አደረጃጀት ያለቸዉ 19 የከተማ አስተዳደሮች አሏት፡፡


**የግንዛቤ ጥያቄ**
አቅጣጫዎችን በምን ዘዴ መለየት እንችላለን?

አንድን አቅጣጫ የሚንለይበት ዘዴ የፀሐይ መውጫ ምሥራቅና የምትጠልቅበት ምዕራብ አቅጣጫን በመጠቀም መለየት እንችላለን፡፡ ፀሀይ የሚትወጣበት አቅጣጫ ምስራቅ ይባላል፡፡ በዚህ መሠረት ፊታችን ወደ ፀሐይ መውጫ አቅጣጫ አዙረን በመቆም ቀኝ እጃችን ደቡብን ፣ ግራ እጃችን ደግሞ ሰሜን አቅጣጫን ያመለክታል ፡፡




**ሥዕል 2.1 አራቱን ዋና ዋና አቅጣጫዎች የሚያመለክት**

አቅጣጫን ማወቅ ከአንድ ቦታ ተነስተን ወዴት እንደምንሄድና የተለያዩ ቦታዎች መገኛ ለመለየት የሚረዳ ነው፡፡ አራቱ አቅጣጫዎችን በመጠቀም ካርታ ላይ የተለያዩ ቦታዎች መገኛ መለየት ይቻላል፡፡ ቀጥሎ የተቀመጠውን ሥዕል በመጠቀም የተለያዩ ቦታዎች መገኛ ለመለየት የሚረዱ አራቱን አቅጣጫዎችን ተመልከት/ቺ፡፡




ሥዕል 2.2 አራቱ ዋናዋና አቅጣጫዎች

**ተግባር 2፡1**

ከታች በ1.3 አራቱን ዋና ዋና አቅጣጫዎችን በሚያሳይ ሥዕል መሰረት ቦና ከአብዲ በስተ ሰሜን አቅጣጫ ይገኛል ፡፡ የተሰጠውን ስዕል እንደ ምሣሌ በመጠቀም የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልስ/ሽ

1. አብዲ ከቦና በየትኛው አቅጣጫ ይገኛል?
2. ጫልቱ ከደራርቱ በየትኛው አቅጣጫ ትገኛለች?
3. ደራርቱ ከጫልቱ በየትኛው አቅጣጫ ትገኛለች?




ሥዕል 2፡3 የተማሪዎች መገኛ አቅጣጫ

## 2.2 አንጻራዊ መገኛ

| |
|---|
| የግንዛቤ ጥያቄ<br>አንጻራዊ መገኛ ማለት ምን ማለት ነው? |

አንጻራዊ መገኛ ማለት አንድ ቦታ ከሌላ ቦታ ጋር በማነጻፀር በየትኛዉ አቅጣጫ እንደሚገኝ የምንለይበት ዘዴ ነው፡፡

ለምሣሌ ፡ ፊንፊኔ ከተማ በሰሜን አቅጣጫ ከሱሉልታ ከተማ፤ በምስራቅ ከለገጣፎ ለገዳዲ ከተማ፤ በምዕራብ ከቡራዩ ከተማ ፤በደቡብ በኩል ደግሞ ከገላን ከተማ ጋር ይዋሰናል ፡፡

## 2.3 ፍጹማዊ መገኛ

ፍፁማዊ መገኛ ማለት የኬክሮስና ኬንትሮስ መስመሮችን ተጠቅመን የአንድን ሀገር ወይም ቦታ ትክክለኛ መገኛ የሚንለይበት ዜደ ነው፡፡ የኬክሮስና ኬንትሮስ መስመሮች በካርታ ላይ ወደተለያዩ አቅጣጫዎች የሚሰመሩ የሐሳብ መስመሮች ናቸው፡፡


### ሀ. የኬክሮስ መስመሮች

የኬክሮስ መስመሮች በካርታ ላይ ከምዕራብ ወደ ምስራቅ ወይም ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ የሚሰመሩ የሃሳብ መስመሮች ናቸው፡፡ እነዚህ የኬክሮስ መስመሮች ከምድር ወገብ በስተሰሜንና በስተደቡብ የሚገኙ ቦታዎችን በዲግሪ ለመለካት የሚጠቅሙ ናቸው፡፡

የኬክሮስ መስመሮች መነሻ መስመር የምድር ወገብ ነው፡፡ የምድር ወገብ መስመር የኬክሮስ መስመሮች መነሻ በመሆኑ በዜሮ ($0^0$) ዲግሪ ላይ ይገኛል፡፡

## ለ. የኬንትሮስ መስመሮች


የኬንትሮስ መስመሮች እንደ ኬክሮስ መስመሮች የአንድ ቦታ መገኛ በዲግሪ ለይቶ የሚያሳይ ነው፡፡ የኬንትሮስ መስመሮች ከትልቁ ሜሪድያን ቦታን በምዕራብና በምስራቅ አቅጣጫ በዲግሪ ለይቶ የሚያሳይ የሀሳብ መስመሮች ናቸው፡፡




ሥዕል 2፡4 የኬክሮስና የኬንትሮስ መስመሮች


ትልቁ ሜሪዲያን የኬንትሮስ መስመሮች መነሻ ሲሆን በዜሮ ዲግሪ ላይ ይገኛል ፡፡ የኬንትሮስ መስመሮች ከሰሜን ወደ ደቡብ ወይም ከደቡብ ወደ ሰሜን የሚሰመሩ የሀሳብ መስመሮች ናቸዉ፡፡ የኬንትሮስና የኬክሮስ መስመሮች የዓለማችን ሀገራትን መገኛ በዲግሪና በአቅጣጫ ለይቶ የሚያሳይ የሀሳብ መስመር ናቸው፡፡

የኬክሮስና ኬንትሮስ መስሮችን በመጠቀም የአንድ ሀገር ወይም ቦታ መገኛ የሚናመለክተው ፍፁማዊ መገኛ ይባላል፡፡




ሥዕል 2፡5 የኬክሮስና የኬንትሮስ መስመሮች

የኬክሮስ እና ኬንትሮስ መስመሮች በካርታ ላይ ትክክለኛ የቦታዎች መገኛ በአቅጣጫ እና በዲግሪ በመታገዝ ያሳያሉ፡፡




ሥዕል 2.6 የኬክሮስ እና ኬንትሮስ መስመሮች

ለምሣሌ ከላይ በሥዕል 1:6 ላይ እንደሚትመለከቱት የሀ ፊደል በ10 ድግሪ ሰሜንና 10 ድግሪ ምስራቅ አቅጣጫ ይገኛል፡፡

በስዕል 2:6 ላይ የተሰጠውን ምሣሌ በማየት የለ ፊደል ትክክለኛ መገኛቸዉን አብራራ/ሪ፡፡

## 2:4 የዞናችን አንጻራዊ መገኛ

ዞናችን በኦሮሚያ ክልል ከሚገኙት ዞኖች ውስጥ አንዱ ነው ፡፡ ዞናችንን ከሚያዋስኑ አጎራባች ዞኖች ጋር በማነጻጸር የዞናችን አንጻራዊ መገኛ የት እንደሆነ ማብራራት እንችላለን፡፡

ለምሣሌ፤ ምስራቅ ሸዋ ዞን በአንጻራዊ መገኛ ዜደ እንደሚከተለው ማብራራት ይቻላል፡፡

## ምሥራቅ ሸዋ ዞን

- ከአርሲ ዞን በስተሰሜን አቅጣጫ ይገኛል
- ከሰሜን ሸዋ ዞንና ከአድስ አበባ ዙሪያ ልዩ ዞን በስተደቡብ አቅጣጫ ይገኛል
- ከደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞን በስተምስራቅ አቅጣጫ ላይ ይገኛል
- ከአፋር ክልላዊ መንግስት በስተምዕራብ ይገኛል፡፡

**ተግባር 2፡2**


ኦሮሚያ ክልል የሚያቅፋቸዉ ዞኖችን የሚያሳይ ካርታ በመጠቀም በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ ከተወያያችሁ በኋላ ማብራሪያ ስጡ፡፡

1. የምትኖሩበት ዞን የሚያዋስኑ የኦሮሚያ ክልል ዞኖች ስም ዘርዝር/ሪ
2. በምስራቅ አቅጣጫ ዞናችሁን የሚያዋስን ዞን ምን ይባላል?
3. አራቱን ዋና ዋና አቅጣጫዎችን በመጠቀም ዞናችሁን የሚያዋስኑ የኦሮሚያ ክልል ዞኖችን ስም ዘርዝር/ሪ

# 2.5 የዞናችን ፍፁማዊ መገኛ

የዞናችን ፍጹማዊ መገኛ የኬክሮስና ኬንትሮስ መስመሮችን በመጠቀም መግለጽ እንችላለን፡፡ ለምሣሌ የክክሮስና

ኬንትሮስ መስመሮች በመጠቀም የፊንፊኔ ከተማ ፍጹማዊ መገኛ በአቅጣጫና በዲግሪ እንደሚከተለዉ ቀርቧል፡፡




ሥዕል 2፡7 ፍፁማዊ የፊንፊኔ ከተማ መገኛ

የኦሮሚያ ክልል ካርታ ላይ ምስራቅ ሸዋ ዞን ከ$7^0$-$9^0$ (ዲግሪ) ኬክሮስ መስመሮች መሀከል ይገኛል፡፡ እንዲሁም ከ$38^0$-$40^0$ (ዲግሪ) ኬንትሮስ መስመሮች መካከል ሆኖ በስተምስራቅ አቅጣጫ ይገኛል፡፡

የኦሮሚያ ክልል ካርታን በመጠቀም የምትኖሩበት ዞን ፍጹማዊ መገኛ መለየት ይቻላል፡፡ እንዲሁም የኬክሮስና የኬንትሮስ መስመሮችን በመጠቀም የተለየዩ የኦሮሚያ ዞኖች መገኛ በአቅጣጫ እና በዲግሪ ማብራራት ይቻላል ፡፡

## 2.6 የዞናችን ታዋቂ ቦታዎች

በዞናችን የተለያዩ ታዋቂ ቦታዎች ይገኛሉ ፡፡ እነሱም ፡

- ተራራዎች
- ወንዞች
- ደኖች
- በገዳ ሥርዓት የተለያዩ ዝግጅቶች የሚካሄዱበት አርዳ ጂላ
- የቱሪስት መስብ ቦታዎች
- ሐይቆች
- ዋሻዎች
- የጥንታዊና የመካከለኛ ዘመን ቤተመንግስት

ሠንጠረዥ 2፡1 በኦሮሚያ ክልል የተለያዩ ታዋቂ ቦታዎች መገኛ

| ተ፣ቁ | ታዋቂ ቦታዎች | መገኛ ቦታ |
|---|---|---|
| 1 | የአባ ጅፋር ቤተመንግሥት | ጅማ ከተማ |
| 2 | የኩምሣ ሞረዳ ቤተመንግስት | ነቀምት ከተማ |
| 3 | የሶፍኡመር ዋሻ | ባሌ ዞን |
| 4 | የቱሉ ዲምቱ ተራራ | ባሌ ዞን |
| 5 | ሆራ-አርሰዲ | ቢሾፍቱ ከተማ |

| | | |
|---|---|---|
| 6 | ጉሚ ጋዮ | ቦረና ዞን |
| 7 | ሚኤ ቦኩ | ጉጂ ዞን |

**ተግባር 2፡3**

**ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ስጥ/ጪ**

1. በዞንናችሁ ዉስጥ ታዋቂ የሆኑ ቦታዎችን ቤተሰቦቻችሁን በመጠየቅ ዘርዚር/ሪ፡፡
2. እነዚህ የዘረዘርካቸውን ታዋቂ ቦታዎች መገኛ ስፍራን ግለፅ/ጭ፡፡

## 2.7 የአዋሳኝ ዞኖች ስምና መገኛ

**የግንዛቤ ጥያቄ**

- ዞናችሁን የሚያዋስኑ የአጎራበች ዞኖች ስም ቤተሰቦቻችሁን በመጠየቅ በክፍል ውስጥ አብራራ/ሪ

አዋሳኝ የሆኑ የዞናችን መገኛ በአራቱ ዋና ዋና አቅጣጫዎች በካርታ ላይ መጥቀስ እንችላለን፡፡ዞናችሁን በተለያየ አቅጣጫዎች የሚያዋስኑ አጎራባች የሆኑ ዞኖች ይገኛሉ ፡፡

## ሠንጠረዥ 2፡2 የኦሮሚያ ክልል የዞኖች ስም ዝርዝር

| ተ.ቁ | የዞኖች ሥም ዝርዝር | ተ.ቁ | የዞኖች ሥም ዝርዝር |
|---|---|---|---|
| 1 | አርሲ | 12 | ምዕራብ ሸዋ |
| 2 | ምዕራብ አርሲ | 13 | ደቡብ ምዕራብ ሸዋ |
| 3 | ባሌ | 14 | ምስራቅ ሐረርጌ |
| 4 | ምስራቅ ባሌ | 15 | ምዕራብ ሐረርጌ |
| 5 | ምስራቅ ወለጋ | 16 | ቦረና |
| 6 | ሆሮጉዱሩ ወለጋ | 17 | ጉጂ |
| 7 | ምዕራብ ወለጋ | 18 | ምዕራብ ጉጂ |
| 8 | ቄለም ወለጋ | 19 | ኢሉአባቦር |
| 9 | ምስራቅ ሸዋ | 20 | ቡኖ በደሌ |
| 10 | ሰሜን ሸዋ | 21 | ጅማ |
| 11 | በፊንፊኔ ዙሪያ የኦሮሚያ ልዩ ዞን | | |
| በዞን ደረጃ የሚጠሩ የከተማ መስተዳድሮች | | | |
| 1 | አዳማ | 11 | ጂማ |
| 2 | አምቦ | 12 | ለገጣፎ ለገ ዳዲ |
| 3 | አሰላ | 13 | ሞጆ |
| 4 | ባቱ | 14 | ነቀምቴ |
| 5 | ቢሻን ጉራቻ | 15 | ሮቤ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 6 | ቡራዩ | 16 | ሰበታ |
| 7 | ቢሾፍቱ | 17 | ሻሸማኔ |
| 8 | ዱከም | 18 | ሱሉልታ |
| 9 | ገላን | 19 | ወሊሶ |
| 10 | ሆለታ | | |

**ተግባር 2፡4**

የሚትኖርበትን ዞን በአራቱም አቅጣጫ የሚያዋስኑ ዞኖች በመለየት ለክፍል አቅርብ/ቢ

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

- መገኛ አንድ ቦታ ወይም ሀገር የሚገኝበት ስፍራ ነው፡፡ እሱም በአንጻራዊና ፍጹማዊ መገኛ ይገለጻል፡፡
- አቅጣጫ አንድ ነገር ወይም ቦታ ከሌላው ቦታ ወዴት እንደምገኝ የሚያመላክት ነው፡፡ ዋና ዋና አቅጣጫዎች፡ ሰሜን፣ ደቡብ፣ ምስራቅና ምዕራብ ናቸው፡፡

## የምዕራፍ 2 ማጠቃለያ ጥያቄዎች

**I. ትክክል የሆነዉን እውነት ስህተት የሆነዉን ሀሰት በማለት መልስ/ሽ፡፡**

1. የምድር ወገብ የኬክሮስ መስመሮች መነሻ ነው፡፡
2. መገኛ ማለት አንድ ቦታ ወይም ሀገር የት እንደሚገኝ የሚያሳይ ነው፡፡
3. ፀሐይ በሰሜን አቅጣጫ ትወጣለች፡፡
4. የኬክሮስ መስመሮች በካርታ ላይ ከሰሜን ወደ ደቡብ የሚሰመሩ ናቸው
5. አቅጣጫዎችን በትክክል ማወቅ የአንድ ቦታ ወይም ሀገር መገኛ ለመለየት ይረዳል

**II. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልስ/ሽ፡፡**

1. የኬክሮስ መስመሮች መነሻ የሆነው የቱ ነው?

   ሀ. ትልቁ ሜሪዲያን

   ለ. የምድር ወገብ

   ሐ. የመጀመሪያ የኬንትሮስ መስመር

   መ. ሁሉም

2. ፊታችሁን ወደ ፀሐይ መውጫ አቅጣጫ ካዞራችሁ ጀርባችሁ የትኛውን አቅጣጫ ያመለክታል?

    ሀ. ሰሜን  ለ. ደቡብ  ሐ. ምእራብ  መ. ሁሉም

3. አቅጣጫዎችን ለይቶ ለማወቅ የሚጠቅመው የቱ ነው?

    ሀ. የአንድ ቦታ ወይም ሀገር መገኛ ለማወቅ

    ለ. የአንድ ቦታ ወይም ሀገር መገኛ አቅጣጫን ለመለየት

    ሐ. ሰዎች ከቦታ ቦታ በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ይጠቀማል

    መ. ሁሉም

4. ፀሐይ የምትወጣበት አቅጣጫ________ ይባላል፡፡

    ሀ. ደቡብ  ለ. ሰሜን  ሐ. ምሥራቅ  መ. ምዕራብ

5. ከሚከተሉት ዓረፍተ ነገሮች እውነት የሆነው የቱ ነው?

    ሀ. ሁለት ዋና ዋና አቅጣጫዎች አሉ

    ለ. ፀሐይ በሰሜን ወጥታ በምዕራብ ትጠልቃለች

    ሐ. አራት ዋና ዋና አቅጣጫዎች አሉ

    መ. መልስ የለውም

6. አንጻራዊ የቦታ መገኛ ለመለየት የሚያገለግል የቱ ነው?

    ሀ. ታዋቂ ተራራዎች  ሐ. ታዋቂ ሐይቆች

    ለ. ፓርኮች  መ. ሁሉም

7. አንጻራዊ መገኛን በትክክል የሚገልጽ የቱ ነው?

ሀ. የቦታዎች ወይም ሀገሮች መገኛ በንጽጽር ለመለየት ይረዳል

ለ. በኬክሮስና በኬንትሮስ መስመሮች ይደገፋል

ሐ. ፍጹማዊ መገኛ ተብሎ ይታወቃል

መ. የቦታዎችን ወይም የሀገሮችን መገኛ በዲግሪ ያሳያል

8. የኬንትሮስ መስመሮችን በማስመልከት ትክክለኛ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. የኬንትሮስ መስመሮች መነሻቸው ትልቁ ሜሪዲያን ነው

**ለ.** የኬንትሮስ መስመሮች መነሻቸው ምድር ወገብ ነው

ሐ. ከምሥራቅ ወደ ምእራብ ይሰመራሉ

መ. ከምእራብ ወደ ምስራቅ ይሰመራሉ

# ምዕራፍ 3

# የተፈጥሮ አከባቢ

## 3.1 የዞናችን አየር ንብረት

### የአየር ሁኔታና አየር ንብረት ልዩነት

**የግንዛቤ ጥያቄ**

በአየር ሁኔታና በአየር ንብረት መካከል ያለው ልዩነት ምንድን ነው?

በየጊዜው የሚለዋወጥ አየር  የአየር ሁኔታ ይባላል::

ለምሳሌ ጠዋት ፀሐያማ፤ ከሰዓት በኋላ ደግሞ ዳመናማ ሲሆን የአየር ሁኔታ ይባላል፡፡ የአየር ሁኔታ በደቂቃዎች፣ በሰዓታት፣ በቀናት፣ በሣምንታት፣ በወራትና በአመታት የሚለዋወጥ የአየር ጠባይ ነዉ፡፡

አየር ንብረት ማለት ደግሞ በረጅም ጊዜ በአንድ ቦታ የሚቆይ የአየር ሁኔታ ማለት ነው፡፡ **ለምሳሌ** በአማካይ

ከሰላሳና ከዚያ በላይ ዓመታት በተደጋጋሚ በቋሚነት የሚቆይ የአየር ሁኔታ ነው፡፡

የአየር ሁነታና የአየር ንብረት ይዘቶች

**የግንዛቤ ጥያቄ**

የአንድ ቦታ የአየር ሁኔታና አየር ንብረት በምን ይገለፃል?

የአንድ አካባቢ የአየር ሁኔታና የአየር ንብረት በመጠነ-ሙቀት፡ በእርጥበት፣ በአየርና በንፋስ ግፊት እና በመሳሰሉት ሊገለጽ ይችላል፡፡

## መጠነ ሙቀት

**የግንዛቤጥያቄዎች**

1. መጠነ-ሙቀት ምንድን ነው?

መጠነ ሙቀት ማለት የአንድ ነገር ወይም የአንድ ቦታ የሙቀት ወይም የቅዝቃዜ መጠንን የሚገለጽ ነው፡፡ የሙቀት መጠን በሁሉም አካባቢ አንድ አይነት መሆን አይችልም፡፡ በአንጻሩ ከጊዜ ወደ ጊዜ፣ ከወቅት ወቅትና ከቦታ ቦታ ይለያያል ፡፡

መጠነ ሙቀት ቴርሞ ሜትር በሚባል መሳሪያ የሚለካ ሲሆን የመለኪያ አሀዱ ደግሞ ዲግሪሴንቲግሪድ ($^{0}$C) ወይም ዲግሪ ፋራናይት ($^{0}$F) ይባላል::

## እርጥበት

| የግንዛቤ ጥያቄ |
| --- |
| እርጥበት ምንድን ነው? |

እርጥበት ማለት በትነት መልክ በአየር ውስጥ የሚገኝ ውሀ ማለት ነው፡፡

በአየር ውስጥ የእርጥበት መጠን የሚጨምረው ከባህር፣ ከዉቅያኖስ፣ ከወንዝ እና ከኩሬ ውሃ በሙቀት አማካይነት በትነት መልክ ወደ አየር ሲጨመር ነው፡፡



ሥዕል 3. 1 የውሃ ትነት

# በተለያዩ ወቅቶች የሚጠበቁ የአየር ፀባይ ልዩነቶች

**የግንዛቤጥያቄ**

በዓመት ውስጥ የሚገኙ አራቱን ወቅቶች ዘርዝር/ሪ፡፡

በዓመት ውስጥ አራት ወቅቶች ይገኛሉ:: እነሱም ክረምት፣ ፀደይ፣ በጋና በልግ ይባላሉ፡፡ በእነዚህ ወቅቶች ያለው የአየር ፀባይ የተለያየ ነው፡፡

ለምሳሌ:- የክረምት ወቅት በአብዛኛው ዳመናማና ዝናባማ ሲሆን፤ የበጋ ወቅት ደግሞ በአብዛኛው ደረቃማና ሞቃታማ ይሆናል፡፡ የበልግና የፀደይ ወቅቶች ደግሞ በብዙ ቦታዎች መጠነኛ የዝናብ መጠን ስለሚኖር የአየሩ ሁኔታም መካከለኛ ይሆናል፡፡

**ተግባር 3.1**

1. በዞናችሁ የክረምትና የበጋ ወቅቶች መጠነ-ሙቀት ልዩነት ላይ ተወያይታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡
2. በዞናችሁ በፀደይና በበልግ ወቅቶች በሚታዩት የዝናብ ሁኔታ ላይ ተወያይታችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

## አየር ንብረትን የሚወስኑ ነገሮች

**የግንዛቤ ጥያቄ**

የአየር ንብረትን የሚወስኑ ነገሮች ምን ምን ናቸው?

የአንድን አካባቢ የአየር ሁኔታ እንዲለዋወጥ የሚያደረጉ ሁኔታዎች የአየር ንብረት ወሳኞች ተብለው ይጠራሉ፡፡ እነዚህም የመሬት ከፍታ፣ ኬክሮስ መስመርና የመሳሰሉ ናቸው፡፡

ከእነዚህ የአየር ሁኔታ ወሳኝ ሁኔታዎች ውስጥ በአካባቢያችን ይበልጥ ጎልቶ የሚታየው የመሬት ከፍታ ልዩነት ነው፡፡ ለምሳሌ፡- የመሬት ከፍታ በጨመረ ቁጥር የዝናብ መጠን የሚጨምር ሲሆን የሙቀት መጠን ደግሞ እየቀነሰ ይሄዳል፡፡ ከዚህ በመነሳት ቦታዎች ደጋ፣ ወይናደጋና ቆላ ተብለው ይመደባሉ፡፡

**ተግባር 3.2**

1. በዞናችሁ በደጋ፣ በወይናደጋና በቆላ አካባቢዎች የሚታስተውለውን የዝናብ ሁኔታ ልዩነት ግለፅ/ጭ፡፡
2. በዞናችሁ በደጋ፣ ወይናደጋና ቆላ አካባቢዎች የሚታስተውለውን የሙቀት ሁኔታ ልዩነት ግለፅ/ጭ፡፡

## 3.2 የተፈጥሮ ሀብት


### የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ሀብት ፍች

| |
|---|
| **የግንዛቤ ጥያቄ**<br>ሀብት ምንድን ነው? |

ሀብት ለኑሮአችን የሚያስፈልጉ ነገሮች ናቸው፡፡ እነዚህ ነገሮች የተፈጥሮና ሰውሰራሽ ሀብቶች ተብለው በሁለት ይከፈላሉ፡፡

| |
|---|
| **የግንዛቤ ጥያቄ**<br>የተፈጥሮ ሀብት ምንድንነው? |

የተፈጥሮ ሀብት ማለት በተፈጥሮ በአካባቢያችን የሚገኙ ሀብቶች ናቸው፡፡ አነዚህም አየር፣ ውሃ፣ የፀሐይ ብርሃን፣ የተፈጥሮ ነዳጅ፣ ዕፅዋት፣ እንሰሳት፣ አፈር፣ ማዕድናትና የመሳሰሉት ናቸው፡፡




ሥዕል 2.3 የተፈጥሮ ሀብቶች

## ሰው ሰራሽ ሀብት

| **የግንዛቤጥያቄ** |
| --- |
| ሰው ሰራሽ ሀብት ምንድን ነው? |

ሰው ሰራሽ ሀብት በሰው ልጆች የተሰሩ ሀብቶች ናቸው፡፡ ከሰው ሰራሽ ሀብቶች ዉስጥ መኖሪያ ቤቶች፣ የቤት ውስጥ እቃዎች፣ ማሽን፣ መኪና፣ ባቡር፣ አውሮፕላን፣ መርከብና የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል፡፡



መኪና



የዉበት እቃዎች



መኖሪያ ቤቶች



ቴሌቭዥን



ስልክ

ሥዕል 3.3 ሰው ሠራሽ ሀብቶች

**ተግባር 3.3**

በሚከተሉት ጥያቄዎች ላይ በመወያየት ለክፍላችሁ አቅርቡ፡፡

1. በዞናችሁ የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶች ምን ምን ናቸው?
2. በዞናችሁ የሚገኙ ሰው ሰራሽ ሀብቶች ምን ምን ናቸው?

## የተፈጥሮ ሀብቶች:- ማዕድናትና የዱር እንስሳት

**የግንዛቤ ጥያቄ**

በዞንህ/ሽ የሚገኙ ማዕድናትና የዱር እንስሳትን ዘርዝር/ሪ፡፡

ማዕድናትና የዱር እንስሳት በተፈጥሮ ሀብት ውስጥ የሚታቀፉ ሀብቶች ናቸው፡፡ ማዕድናት በመሬት ውስጥ የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶች ሲሆኑ እነዚህም እንደ ወርቅ፣ ብር፣ ብረት፣ አልማዝ፣ የከሰል ድንጋይ፣ ድኝ እና የመሰሰሉትን ያቅፋሉ፡፡

የዱር እንስሳት ደግሞ በተለያዩ አካባቢዎችና ሁኔታዎች ከሰው ሳይላመዱ ርቀው የሚኖሩ እንሰሳት ናቸው፡፡ የዱር እንሰሳት በጨካ፣ በውሃ፣ በፓርኮችና በመሳሰሉት አካባቢዎች እራሳቸዉን አላምደዉ ይኖራሉ፡፡ የዱር እንሰሳት ለመኖር የሚያስፈልጋቸው እንደ ምግብ፣ መጠለያ ቦታ፣ ውሃና የመሳሰሉትን በራሳቸው ይፈልጋሉ፡፡

### በዞናችን የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶች ጥቅሞችና ቱሩፋቶች

የተፈጥሮ ሀብቶች ለምግብ፣ ለሀይል ማመንጫና የተለያዩ ቁሳቁሶችን ለመስራት ይጠቅማሉ፡፡ ሰዎች ምግባቸውን ከዕፅዋትና ከእንሰሳት ያገኛሉ፡፡

ከተፈጥሮ ሀብቶች ውስጥ የከሰል ድንጋይና የተፈጥሮ ጋስ ሙቀትና ብርሃን ለማመንጨት ይጠቅማሉ፡፡ ስለዚህ የተፈጥሮ ሀብቶችን መንከባከብ ይገባል፡፡

የተፈጥሮ ሀብቶች የተለያዩ ቱሩፋቶችንም ያስገኛሉ፡፡ ከእነዚህ ቱሩፋቶችም የመዝናኛ፣ የምርምር፣ የሥነ-ውበትና የባህል ሊሆኑ ይቻላሉ፡፡

በመሆኑም ለተፈጥሮ ሀብት የሚደረግ እንክባካቤ ሀብቶቹ እንዳይጎዱና እንዳይባክኑ በማድረግ ለረጅም ጊዜ እንዲያገለግሉ ለማድረግ ይጠቅማል፡፡

ተግበር 3.4

1. በዞናችሁ የሚገኙ የዱር እንሰሳት ምን ምን ናቸው?
2. በዞናችሁ ውስጥ የሚገኙ ማዕድናትን ዘርዝር/ሪ::
3. በዞናችሁ የሚገኙ የተፈጥሮ ሀብት ቱሩፋቶችን ዘርዝር/ሪ፡፡

# 3.3 የተፈጥሮ ሀብት አስፈላጊነት

**የግንዛቤ ጥያቄ**

1. የተፈጥሮ ሀብት ለምን ያስፈልጋል?
2. የተፈጥሮ ሀብት ለዞናችን ልማት ምን ያበረክታል?

የተፈጥሮ ሀብት ህይወት ላላቸው ነገሮች በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ የተፈጥሮ ሀብት የተለያዩ ጥቅሞችን ያስገኛል፡፡ ከእነዚህ ጥቅሞች ዉስጥ፡-

- ለገቢ ምንጭ
- ለሀይል ምንጭ
- ለውሃና አካባቢ ንጽህና
- ለምግብ ምንጭ
- ለእንሰሳት መጠለያ
- ለአፈር ልማትና እንክባካቤና የመሳሰሉት መጥቀስ ይችላል፡፡

በመሆኑም የተፈጥሮ ሀብቶችን መንከባከብና በአግባቡ ጥቅም ላይ ማዋል  የሰው ልጆችን ኑሮ ለመሻሻል እጅግ በጣም ጠቃሚ ነው፡፡

## የተፈጥሮ ሀብቶች ውድመት ምክንያቶችና ተፅዕኖ

**የግንዛቤ ጥያቄ**

የተፈጥሮ ሀብት ውድመት ማለት ምን ማለት ነው?

የተፈጥሮ ሀብት ውድመት ማለት በተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤና ጥበቃ እጦትና ያለአግባብ በመጠቀም በተፈጥሮ ሀብት ላይ የሚደርስ ጉዳት ማለት ነው፡፡

**የግንዛቤ ጥያቄ**

ለተፈጥሮ ሀብት ውድመት ምክንያት የሆኑት ተግባራት ምን ምን ናቸው?

ለተፈጥሮ ሀብቶች ውድመት ምክንያት ከሆኑት ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸዉ፡፡

- የህዝብ ቁጥር መጨመርና የከተሞች መስፋፋት፣
- ያለአግባብ መጠቀም፣
- የደን ምንጠራና ቃጠሎ፣
- የኢንዱስትሪዎች እድገትና መስፋፋት፣
- የአፈር መሸርሸር፣ እጥበትና የመሳሰሉት ናቸው ፡፡

ሥዕል 3.4 የደን ምንጣሮና ከከተሞች የሚወጣ ቆሻሻ

**የግንዛቤ ጥያቄ**

በተፈጥሮ ሀብቶች ውድመት ምክንያት ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮች ምን ምን ናቸው?

በተፈጥሮ ሀብቶች ውድመት ምክንያት ሊፈጠሩ ከሚችሉ አሉታዊ ነገሮች ዉስጥ ዋና ዋናዎቹ፡-

- የጤና ችግር
- ረሃብ
- የኢኮኖሚ ችግሮች እና የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል

## የተፈጥሮ ሀብቶችን መጠበቅና መንከባከብ

**የግንዛቤ ጥያቄ**

የተፈጥሮ ሀብትን በምን መንገድ መንከባከብ እንችላለን?

# የአፈር እንክባካቤ

**የግንዛቤ ጥያቄ**

አፈርን በምን አይነት ዘዴ መንከባከብ እንችላለን?

የአፈር እንክብካቤ ዘዴዎች ብዙ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ ዋና ዋናዎቹ፡-

- አግድም ማረስ፣
- ችግኝ መትከል፣
- እርከን መስራት፣
- የዕፅዋት ተረፈ ምርቶችን በእርሻ ማሳ ላይ በመውሰድ ለማዳበሪያነት መጠቀም፣
- የግጦሽ መሬትን ከሚገባው በላይ አለማስጋጥና በመሳሰሉት መንገዶች አፈርን መንከባከብ ይቻላል፡፡





ሥዕል 3.4 እርከን የተሰራበትና አግድም የታረሰ መሬት

**ተግባር 3.5**

በአካባቢህ/ሽ የሚስተዋለውን የአፈር እንክብካቤ ሁኔታ ወላጅህን/ሽን በመጠየቅ ለክፍል ጓደኞችህ አቅርብ/ቢ::

## የውሃ እንክብካቤ

**የግንዛቤ ጥያቄ**

ከውኃ እንክብካቤ ዘዴዎች ውስጥ የሚታውቀውን/ቂውን ተናገር/ሪ::

ውሃን የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም መንከባከብ ይቻላል፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ችግኞችን መትከል፣
- የዝናብ ውሃን በማጠራቀም መጠቀም፣
- ቆሻሻን ውሃ ዉስጥ አለመጣል፣
- ውሃን በቁጠባ በመጠቀምና በመሳሰሉት




ሥዕል 4.5 ችግኝ መትከልና የዝናብ ውሃ ማጠራቀም

## የደን እንክብካቤ

| **የግንዛቤ ጥያቄ** |
| --- |
| ደን እንዴት ይንከባከባል? |

ደንን በተለያዩ ዘዴዎች መንከባከብ የሚቻል ሲሆን፤ ከእነዚህ ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው ፡፡

- ለደን ጥበቃ በማድረግ፣
- በደን ጥበቃና እንክብካቤ የህብረተሰቡን ግንዛቤ በማጎልበት
- ችግኝ በመትከል
- በደን ጥበቃና እንክብካቤ ላይ በገዳ ስርዓት የተደነገጉትን ተግባራዊ በማድረግና በመሳሰሉት

### የተፈጥሮ ሀብቶችን መጠበቅና መንከባከብ ለምን ያስፈልጋል?

የተፈጥሮ ሀብቶችን መጠበቅና መንከባከብ በርካታ ጥቅሞች ያሉት ሲሆን ዋና ዋናዎች የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የተፈጥሮ ሚዛንን ለመጠበቅ፣
- ለቀጣይ ትውልድ እንድተላለፍ ለማድረግ፣
- በቀጣይነት ለመጠቀም ይረዳል፡፡

## 3.4 ቆሻሻን ማስወገድ

**የግንዛቤ ጥያቄ**

በትምህርት ቤትህ/ሽ ውስጥ ቆሻሻ የሚወገደው በምን ዓይነት ዘዴ ነው?

ቆሻሻ በደረቅ ወይም በፈሳሽ መልክ ሊኖር ይችላል፡፡ እነዚህ ቆሻሻዎች አከባቢያችን ይበክላሉ፡፡ አከባቢያችንን ልበክሉ የሚችሉ ቆሻሻዎች ከተለያየ ቦታ ሊወጡ ይችላሉ፡፡ እነዚህም፡-

- መኖሪያ ቤቶች
- የገበያ ቦታዎች
- ከተሞችና
- ፋብሪካዎች በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው ፡፡

ሥዕል 3.6 ከተለያየ ቦታ የሚወጣ ቆሻሻ

በአከባቢያችን ከሚስተዋሉ ዋና ዋና ችግሮች ውስጥ ቆሻሻን ባልተገባ ቦታ መጣል አንዱ ነው። ይህንን ችግር ለመቅረፍ ቆሻሻን በአግባቡ ማስወገድ አስፈላጊ ነው።

በመሆኑም የሚከተሉትን መልካም ተሞክሮዎችና ተግባራትን ተግባራዊ በማድረግ ቆሻሻን ማስወገድ ይቻላል። ከእነዚህ መልካም ተግባራት ውስጥ የሚከተሉት በዋናነት የሚጠቀሱ ናቸው።

- ቆሻሻ መጣያ ቦታዎችን በማዘጋጀት መጠቀም፣
- የዕፅዋት ተረፈ ምርትን በኮምፖስት መልክ ለማዳበሪያነት መጠቀም፣
- የተለያዩ የፕላስቲክ እና የወረቀት ቆሻሻዎችን መልሰዉ መጠቀም፣
- ከተለያዩ ቦታዎች የሚወጡ ፍሳሽ ቆሻሻዎችን በአግባቡ በማስወገድና የመሳሰሉት ናቸው።



ቆሻሻን ለይቶ በተገቢው ቦታ ማጠራቀም



የተጣሉ ፕላስቲኮችን ለሌላ አገልግሎት መዋል





የሚጣሉ ቆሻሻዎችን በኮምፖስት መልክ መጠቀም

ሥዕል 3.7 ቆሻሻን ለተለያየ አገልግት ማዋል

**ተግባር 3.6**

አከባቢን ልበክሉ ከሚችሉ ቆሻሻዎች እንደገና ጥቅም ላይ ልዉሉ የሚችሉትን አብራሩ/ሪ::

## 3.5 ቆሻሻን ተገቢ ባልሆነ መንገድ ማስወገድ የሚያስከትለው ተፅዕኖ

ቆሻሻን ተገቢ ባልሆነ መንገድ ማስወገድ በጤና ላይ ከፍተኛ ጉዳት ሊያስከትል ይችላል፡፡ ይህ ቆሻሻ፣ አፈር፣ ውሃ እና አየርን በመበከል በሰዎችና በሌሎች ህይወት ባላቸዉ ነገሮች ላይ የሚከተሉትን ችግሮች ያመጣል፡፡

- ለተለያዩ ተላላፊና ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች መነሻ ይሆናል፣
- በአካል እድገትና ግንባታ ላይ ችግር ያመጣል፣
- የአተነፋፈስ ሥርዓትን ማዛባትና የመሳሰሉት ናቸው ፡፡



ሥዕል 3.8 ከቤትና ከፋብሪካ ውስጥ በሚወጣ ቆሻሻ የሚመጣ ተፅዕኖ

በተመሳሳይ መልኩ ባልተገባ መንገድ የሚጣል ቆሻሻ ውሃ ውስጥ የሚኖሩ እንስሳትንም በእጅጉ ይጎዳል፡፡



ሥዕል 3.9 በውሃ ውስጥ የተጣለ ቆሻሻ

ባልተገባ መንገድ በሚጣል ቆሻሻ ሊደርስ የሚችለውን ችግር ለማስቀረት የአካባቢያችንን ንጽህና መጠበቅ አስፈላጊ ነው፡፡

**የግንዛቤ ጥያቄ**

የአካባቢን ንፅህና መጠበቅ የሚያስገኘው ጥቅም ዘርዝር/ሪ፡፡

የአካባቢ ንጽህና መጠበቅ የተለያዩ ጥቅሞችን ያስገኛል፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው ፡-

- አከባቢን ከተለያዩ በሽታዎች ነፃ ያደርጋል፣
- ህይወት እንዳይናጋ ያደርጋል፣
- ምርታማነትን ለመጨመር ይረዳል፣
- ለህክምና የሚወጣ ወጪ ይቀንሳል፣
- ለአከባቢ ውበት፣ ምቾትና ለመሳሰሉት ይጠቅማል

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

- በአጭር ጊዜ ውስጥ የሚለዋወጥ የአየር ፀባይ የአየር ሁኔታ ይባላል፡፡
- ለረጅም ጊዜ ሳይቀያየር የሚቆይ የአየር ፀባይ የአየር ንብረት ይባላል፡፡
- የአንድ ነገር ሙቀትና ቅዝቃዜ መጠነ ሙቀት ይባላል፡፡
- አራቱ ወቅቶች፤ ክረምት፣ ፀደይ፣ በጋና በልግ ናቸው፡፡
- ሀብቶች በሁለት ይከፈላል፡፡ እነርሱም፤ የተፈጥሮና ሰው ሰራሽ ነቸው፡፡

## የምዕራፉ መልመጃ

### I. እውነት ወይም ሐሰት በማለት መልስ/ሺ፡፡

1. መጠነ ሙቀት ማለት የነገሮች ሙቀትና ቅዝቃዜ ነው፡፡
2. እርጥበት ከአየር ፀባይ ይዘቶች ውስጥ አንዱ ነው፡፡
3. የመሬት ከፍታ የአየር ንብረትን ይወስናል፡፡
4. እንስሳት የተፈጥሮ ሀብቶች ናቸው፡፡
5. የድንጋይ ከሰል ሰው ሰራሽ ሀብት ነው፡፡

### II. ትክክለኛዉን መልስ የያዘውን ፍደል ምረጥ/ጭ፡፡

6. በየጊዜው የሚለዋወጥ የአየር ሁኔታ ምን ተብሎ ይጠራል?

   ሀ. የአየር ሁኔታ　　　ሐ. መጠነ ሙቀት

   ለ. የአየር ንብረት　　　መ. ነፋስ

7. በአንድ አከባቢ ለረጅም ጊዜ የሚስተዋል የአየር ፀባይ -------ይባላል፡፡

   ሀ. ነፋስ　　　ሐ. የአየር ንብረት

   ለ. የአየር ሁኔታ　　　መ. መጠነ ሙቀት

8. ከሚከተሉት ውስጥ በትክክለኛ መንገድ ቆሻሻን የማስወገድ ዘዴ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. ወረቀትን ቀዳዶ መጣል

ለ. ሊበሰብሱ የሚችሉ ቆሻሻዎችን ለማዳበሪያነት መጠቀም

ሐ. የተለያዩ የፕላስቲክ ቆሻሻዎችን በየቦታው መጣል

መ. የኤሌክትሮኒክስ ስብርባሪ ቆሻሻዎችን በየቦታው መጣል

9. ቆሻሻን ሊቀንስ የሚችል ዘዴ የቱ ነው?

ሀ. የተጣሉ ቆሻሻዎችን በድጋሚ መጠቀም

ለ. ከተለያዩ ቦታዎች የሚወጡ ፍሳሽ ቆሻሻዎችን በተወሰነ ቦታ መሰብሰብ

ሐ. ቆሻሻ ሊሆኑ የሚችሉትን ነገሮች መቀነስ

መ. ሁሉም መልስ ነው

10. ቆሻሻን ትክክለኛ ባልሆነ መንገድ የማስወገድ ተፅዕኖ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. ህይወት ያላቸውን ነገሮች ጤና ማናጋት

ለ. የዉሃ ብክለት

ሐ. የአፈር ብክለት

መ. ሁሉም መልስ ነው

# ምዕራፍ 4

# ማህበራዊ አከባቢ

## 4.1 የባህል ብዝሃነት

| |
|---|
| የግንዛቤ ጥያቄዎች |
| ባህል ማለት ምን ማለት ነው? ባህል በምን ይገለጻል? |

ባህል የአንድ ህብረተሰብ ማንነት መገለጫ ነው፡፡ ባህል ለረጅም ጊዜ የሚገኝ ልምድ ሆኖ ለዘመናት ከትውልድ ወደ ትውልድ ስተላለፍ የቆየ ነው፡፡ በአጠቃላይ ባህል የአንድ ህብረተሰብ የዘመናት ልምድና ተጠናክረው ሊቀጥል የሚችል ቱፊት ነው፡፡

የተለያዩ የማህበረሰብ ባህል ተመሳሳይ ወይም አንድ ሊሆን አይችልም ፡፡ ምክንያቱም በተለያዩ የመኖሪያ ቦታቸው ያካበቱት ልምዶች ስለሚለያይ ነው፡፡ ከቆይታ በኃላ ማህበረሰቦች ያካበቱት የተለያዩ ልምዶች የማህበረሰቡ

የአኗኗር ሁኔታ እንዲለያይ አድርጓል ፡፡ ይህ የአኗኗር ልዩነት መኖር ለባህል ብዙሃነት ዋና ምክንያት ሆኑዋል፡፡ የአንድ ማህበረሰብ ባህል በተለያዩ ነገሮች ይገለጻል፡፡ እነሱም፡-

- በአለባበስ
- በምግብ ዝግጅት
- በእርቅ ሥርዓት
- በአመልኮ ሥርዓት
- ደስታን የሚያበስሩበት እና
- ሐዘንን በሚያካሂዱበት ሥርዓቶች ይገለጻል

## የአለባበስ ባህል

| |
|---|
| **የግንዛቤ ጥያቄ**<br>በአካባቢያችሁ የተለመደ የአለባበስ ባህል ከጓደኞቻችሁ ጋር ከተወያያችሁ በኋላ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ ፡፡ |

የኦሮሞ ብሄረሰብ የራሳቸው የሆነ በተለያዩ ዝግጅቶች ላይ የሚለበሱ የአለባበስ ስርዓት አላቸው፡፡ ለምሣሌ የኦሮሞ የአለባበስ ባህል ቀጥሎ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡



ሥዕል 4፡1 የኦሮሞ ባህላዊ አለባበስ

**ተግግባር 4፡1**

በዞናችሁ ውስጥ የሚከናወኑ ታዋቂ ባህላዊ ሥርዓቶችን ቤተሰቦቻችሁን በመጠየቅ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡፡

## የአመጋገብ ባህል

**የግንዛቤ ጥያቄ**

በሚትኖርበት ዞን ታዋቂ የባህል ምግቦችን ዘርዝር፡፡

የአንድ ማህበረሰብ ባህል ከሚገለፅባቸው ነገሮች ውስጥ አንዱ የአመጋገብ ስርዓት ነው፡፡ ይህ ማለት የምግብ ኣዘገጃጀት እና አይነቶችን ያካትታል ፡፡ በተለያዩ የኦሮሚያ ዞኖች ማህበረሰቡ የራሳቸዉ የሆነ የአመጋገብ ባህል አላቸዉ፡፡ ተመሳሳይ የሆነ የአመጋገብ ባህል አለመኖራቸዉ ለባህል ብዝሀነት መኖር ምክንያት ሆነዋል፡፡ ለምሣሌ ፡- የኦሮሞ ብሄረሰብ የአመጋገብ ባህልና የተለያዩ የምግብ አይነቶች እንደሚከተለው ቀርቧል ፡፡





**በሥዕል 4፡2 የተለያዩ የኦሮሚያ ዞኖች የምግብ ዓይነቶች**

**ተግባር 4፡2**

በሚትኖርበት ዞን ታዋቂ የሆኑ የምግብ ዓይነቶች ቤተሰቦቻችሁን በመጠየቅ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ

## የእርቅ ሥርዓት

**የግንዛቤ ጥያቄ**

የእርቅ ሥርዓት ወይም ባህል ማለት ምን ማለት ነው?

የኦሮሞ ብሄረሰብ የራሳቸው የሆነ የግጭት አፈታትና የእርቅ ስርዓት አላቸው ፡፡ ለምሳሌ የኦሮሞ ብሄረሰብ በገዳ ስርዓት አማካይነት በሰላማዊ መንገድ ግጭቶችን በመፍታት እርቅ ያወርዳል ፡፡



ሥዕል 4፡3 በገዳ የእርቅ ሥርዓት ሲከናወን

**ተግባር 4፡3**

በቡድን በመደራጀት በአካባቢያችሁ የሚከሰቱት ግጭቶችን በሰላማዊ መንገድ እንዴት እንደሚፈቱ በተግባር ሰርታችሁ አሳዩ፡፡

## የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ ባህል

**የግንዛቤ ጥያቄ**

በሚትኖርበት ዞን የሚታወቁ ባህላዊ የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ ግለፅ/ጪ፡፡

የኦሮሞ ብሂረሰብ በተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ ይታወቃል፡፡ ምክንያቱም የገዳ ስርዓት ለአካባቢ ጥበቃ ራሱን የቻለ ህግ ስላለው ነው፡፡

**ለምሣሌ፡-**

- ቀጥ ያለ እና ውብ ሆኖ በማደግ ላይ ያለ ዛፍ አይቆረጥም
- አድጎ ለሰዎች መጠለያ የሚሆን ዛፍ አይቆረጥም
- እንደ ምልክት  የሚያገለግል ዛፍ አይቆረጥም፡፡

**ተግባር 4.4**

በሚትኖርበት ዞን የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ በምን ዓይነት እንደሚከናወን ቤተሰቦቻችሁን ጠይቃችሁ ለክፍል አቅርቡ

## 4.2 የዞናችን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ

**የግንዛቤ ጥያቄ**

በሚትኖርበት ዞን ነዋሪዎች በአብዛኛው ምን በመስራት ይታወቃል?

የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ማለት ምርትን ማምረት፣ ማሰራጨትና የተለያዩ አገልግሎቶችን መስጠት ያካትታል፡፡ የሚትኖርበት ዞንና ለሎች የኦሮሚያ ዞኖች በተለያዩ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ልከናወኑ ይችላሉ፡፡

እነሱም:- የግብርና ሥራ፣ አሣ እርባታ፣ ንግድ፣ ማዓዓዣ፣ ቱሪዝም፣ ኢንዱስትሪና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

**ለምሣሌ፡- የሚከተሉትን የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ማመዛዘን ትችላላችሁ**



የሆቴል አገልግሎት



የግብርና ሥራ



የሽመና ሥራ



የብረታ ብረት ሥራ

**ሥዕል 4፡4 የተለያዩ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች**

በዞናችሁ ካሉት ከተለያዩ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ውስጥ አንዱ የንግድ ሥራ ነው ፡፡ የንግድ ሥራ ግዥና ሽያጭን ያካትታል፡፡ ግዥና ሽያጭ የሚከናወንበት ቦታ ገበያ በመባል ይታወቃል ፡፡



ሥዕል 4.5 የገበያ ማዕከል

በዞናችሁ የሚታወቀው ሌላ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የመጓጓዣ አገልግሎት ነው፡፡ የመጓጓዣ አገልግሎት ሰዎችና እንስሳትን ከቦታ ቦታ ለማንቀሳቀስ ይረዳል፡፡

**የግንዛቤ ጥያቄ**

የአካባቢያችሁ ሰዎች ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ለመጓጓዝ የሚጠቀሙበት ምንድነዉ?

የተለያየ የመጓጓዣ ዓይነቶች ይኖራሉ፡፡ እነሱም ዘመናዊና ባህላዊ የመጓጓዣ ዓይነቶች ናቸዉ፡፡



ሥዕል 4፡6 ባህላዊ የመጓጓዣ ዓይነቶች



ሥዕል 4.7 ዘመናዊ የመጓጓዣ ዓይነቶች

**ተግግባር 4፡5**

1. በዞናችሁ የሚገኙ ባህላዊ የመጓጓዣ ዓይነቶች ስም ዘርዝሩ
2. በአካባቢያችሁ ሰዎችንና የተለያዩ እቃዎችን ለማጓጓዝ የሚረዱ የመጓጓዣ ዓይነቶች ዘርዝሩ፡፡
3. በአካባቢያችሁ አብዛኛውን ጊዜ ለገበያ የሚቀርቡ የተፈጥሮ ሀብት ውጤቶች ቤተሰቦቻችሁን ጠይቃችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ ፡፡

ለሀገር ምጣኔ ሀብት እድገት የተለያዩ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ከፍተኛ ሚና አለው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች በተፈጥሮ ሀብት ላይ ጉዳት ሊያደርሱ ይችላሉ፡፡

**ለምሣሌ፡-**

- የእርሻ ማሳ ለማስፋፋት የተፈጥሮ ደን መመንጠር
- ከፋብሪካ የሚወጡ ፍሳሽ ቆሻሻዎችና ጪስ አካባቢን ይበክላሉ፡፡
- ከመኪና የሚወጣ ጪስ አካባቢን ይበክላል
- የዱር አራዊቶች መጠለያ ሊያሳጣ ይችላል
- የአየር ንብረት ለውጥ ሊያመጣ ይችላል





ሥዕል 4፡8 የሰደድ እሣት እና ከፋብሪካ የሚወጣ ጪስ

**ተግባር 4፡6**

በአካባቢያችሁ በተለያዩ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ምክንያት በተፈጥሮ ሀብት ላይ የደረሱ ጉዳቶችን ዘርዝሩ፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

- ባህል የአንድ ብሂረሰብ ማንነት መገለጫ ነው፡፡
- ባህል በአለባበስ፣ በአመጋገብ፣ በእርቅ፣ በደስታና በሀዘን ይገለጻል፡፡
- የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ሂደት ማምረትን፣ ማሰራጨትን፣ አገልግሎት መስጠትንና የመሳሰሉትን ያካትታል፡፡
- ይህ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ግብርና፣ ዓሳ እርባታ፣ የሆቴል አግልግሎት፣ መጓጓዣ፣ ቱሪዝምና የመሳሰሉት ናቸው›

## የምዕራፉ ማጠቃለያ ጥያቄዎች

### I ትክክል የሆነዉን እውነት ስህተት የሆነዉን ሀሰት በማለት መልስ/ሽ

1. የአካባቢያችን ሀብቶች ተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ በመባል ይታወቃሉ፡፡
2. ከባህል መገለጫዎች ውስጥ አንዱ የአለባበስ ስርዓት ነው፡፡
3. ከኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴዎች አንዱ የግብርና ሥራ ነው፡፡
4. ባህል የአንድ ህዝብ ማንነት መገለጫ ነው፡፡
5. የአንድን ህብረተሰብ ባህል በባህላዊ አለባበስ መለየት ይችላል፡፡

### II ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልስ/ሽ

6. የአንድ ህብረተሰብ ባህል የሚገለፅ የቱ ነው?

ሀ. የአለባበስ ባህል ለ. የአመጋገብ ባህል

ሐ. የአምልኮ ሥርዓት መ. ሁሉም

7. ከኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ውስጥ የግዥና ሽያጭ አገልግሎት የሚከናወንበት ቦታ ምን ይባላል?

ሀ. ንግድ ለ. ግብርና ሥራ ሐ.ገበያ መ. ፋብሪካ

8. በአካባቢያችሁ የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ የሆነው የቱ ነው?

ሀ. እርከን መስራት ሐ.ችግኝ መትከል

ለ. አግድም ማረስ መ. ሁሉም

9. የሀገራችን ህዝቦች በስፋት የተሰማሩበት የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የትኛው ነው?

ሀ. ኢንዱስትሪ ሐ. ቱሪዝም

ለ. ግብርና መ.ቴክኖሎጂን በማስፋፋት

10. ከሚከተሉት ውስጥ የተፈጥሮ ሀብት የሆነው የቱ ነው?

ሀ. አየር ንብረት ለ. ውሃ ሐ. ደን መ. ሁሉም

# ምዕራፍ 5

# ትኩረት የሚሹ ጉዳዮች

## 5.1 የመንገድ ላይ ጥንቃቄ

**የግንዛቤ ጥያቄ**

1. በመኪና መንገድ ላይ ስንሄድ ማድረግ የሚገባን ጥንቃቄ ምንድነው?
2. ልከበሩ የሚገቡ የመንገድ ትራፊክ ደንቦች ምን ምን ናቸው ?

የመንገድ አጠቃቀምና ጥንቃቄ ማለት በመንገድ ላይ ስንጓዝ ከተለያዩ የትራፊክ አደጋዎች ራሳችንን ለመከላከል የምናደርጋቸው ጥንቃቄዎች ማለት ነው፡፡

በመንገድ ላይ በተለያየ ምክንያት የትራፊክ አደጋዎች ሊደርሱ ይችላሉ፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ዋና ዋናዎቹ፡-

- መንገድ ስንሻገር ግራና ቀኝ አይቶ በጥንቃቄ አለመሻገር፣
- አሽከርካሪዎች ጥንቃቄ አለማድረግ፣
- እንስሳትን ያለጥንቃቄ መንገድ ላይ መንዳት፣
- በከባድ ዝናብ ምክንያት በድንገት የሚደርስ ጎርፍና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

ከላይ ከተዘረዘሩ የአደጋ ምክንያቶች የተነሳ የተለያዩ አደጋዎች ሊደርሱ ይችላሉ፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የህይወት መጥፋት፣
- የሀብት መውደም፣
- በእንሰሳት ላይ ጉዳት መድረስ፣
- የአካል መጉደልና የመሳሰሉት




ሥዕል 5.1 የመኪና አደጋ

**የግንዛቤ ጥያቄ**

የመንገድ ትራፊክ አደጋን እንዴት መከላከል ይችላል?

የመንገድ የትራፊክ አደጋዎችን በተለያዩ መንገዶች መከላከል ይቻላል፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

- የመኪና መንገድ ስሻገሩ ቀኝና ግራን በማየት በጥንቃቄ መሻገር፣
- በመኪና መንገድ ላይ አለመጫወት፣
- የትራፊክ ደንቦችን ተገንዝቦ ተግባራዊ ማድረግ፣
- መንገድ ስናቋርጥ በዜብራ ምልክት ላይ መሻገር፣
- በመኪና መንገድ ላይ የግራ እጅ አቅጣጫን ይዞ መሄድና የመሳሰሉት ይጠቀሳሉ፡፡



ሥዕል 5.2 በዜብራ ምልክት ላይ መሻገር

**ተግባር 5.2**

1. ለመንገድ ትራፊክ አደጋ ምክንያት ከሆኑት ውስጥ አራቱን ጥቀስ/ሽ፡፡
2. በመንገድ አጠቃቀም ወቅት ልተኮርባቸው የሚገቡ የትራፊክ ደንቦች ምን ምን ናቸው?
3. በመኪና መንገድ ጎን ስትጓዝ/ዢ በየትኛውን አቅጣጫ መሄድ አለብህ/ሽ፡፡

## 5.2 ኤች አይ ቪ /ኤድስ

**የግንዛቤ ጥያቄ**

ኤች አይ ቪ ምንድን ነው? ኤድስ ምንድንነዉ?

ኤች አይ ቪ ነጭ የደም ህዋስን በመጉዳት ኤድስ የሚባል በሽታን የሚያስከትል ቫይረስ ነው፡፡ ነጭ የደም ህዋስ ሰውነታችንን ከበሽታ የሚከላከሉ ናቸው፡፡ እነዚህ ህዋሳት በኤች አይ ቪ ሲጠቁ የሰውነታችን በሽታን የመከላከል አቅም ይደክማል፡፡

ኤድስ የሚባለው ደግሞ በኤች.አይ.ቪ. ቫይረስ ምክንያት የሚመጣ በሽታ ነው፡፡ ይህ በሽታ እስከአሁን ድረስ መድሃኒት ያልተገኘለት በሽታ ነው፡፡ ስለዚህ በኤድስ በሽታ

የተያዘ ሰው ልድን አይችልም ፡፡ ይሁንና በጤና ተቋማት በሽታውን በመቋቋም እድሜን ማስረዘም የሚያስችል መድሃኒት ይሰጣል ፡፡

የኤድስ በሽታ ቫይረሱ ካለበት ሰው ወደ ሌላ ሰው በተለያየ መንገዶች ይተላለፋል፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡፡

- በደም ንክኪ፣
- የተለያዩ ስለት ያላቸውን ነገሮች በጋራ በመጠቀም፣
- ከእናት ወደ ልጅ፡-
    - ✓ ከወሊድ በፊትና
    - ✓ በወሊድ ጊዜ

የኤች አይ ቪ ቫይረስ በመጨባበጥ፣ አብሮ በመጫወት፣ አብሮ በመማር፣ የተለያዩ ዝግጅቶች አብሮ በመካፈል፣ አብሮ በመብላት እና በመሳሰሉት ልተላለፍ አይችልም፡፡

**ተግባር 5.2**

1. በኤች. አይ.ቪ.ና በኤድስ መካከል ያለውን ልዩነት ግለጽ/ጪ፡፡
2. የኤች አይ ቪ ቫይረስ በደማቸው ዉስጥ ያላቸው ሰዎች እድሜያቸውን ለማስረዘም ምን ማድረግ አለባቸው?
3. የኤች አይ ቪ ቫይረስ የሚተላለፍባቸውን መንገዶች ዘርዝር /ሪ፡፡

## የኤች አይ ቪ ኤድስ በሽታ ምልክቶች

**የግንዘቤ ጥያቄ**

በኤች አይ ቪ በሽታ የተያዙ ሰዎች ምን ምን ምልክቶችን ያሳያሉ?

በኤድስ በሽታ የተያዙ ሰዎች ምንም አይነት የበሽታ ምልክት ሳያሳዩ የኤች አይ ቪ ቫይረስን ማስተላለፍ ይችላሉ፡፡

እነዚህ ሰዎች በበሽታው መያዛቸው የሚታወቀው የደም ምርመራ ሲያደርጉ ብቻ ነው፡፡ በህደት ግን በቫይረሱ የተያዙ ሰዎች የሚከተሉትን ምልክቶች ሊያሳዩ ይችላሉ፡-

- የሰውነት ሙቀት በተከታታይ መጨመር፣
- ለረጅም ጊዜ የሚቆይ የራስ ምታት፣
- ለረጅም ጊዜ የሚቆይ ደረቅ ሳል፣
- የሰውነት ክብደት በፍጥነት መቀነስ፣
- ኃይል መጣትና የድካም ስሜት መሰማት፣
- ተቅማጥ፣
- የአፍ ውስጥ ቁስለትና የመሳሰሉት

## የምዕራፍ 5 የመልመጃ ጥያቄዎች

I.ትክክል የሆነዉን እውነት ስህተት የሆነዉን ሀሰት በማለት መልስ/ሺ::

1. ሰዎች በመኪና መንገድ ላይ ሲጓዙ ግራ አቅጣጫ በመያዝ መጓዝ አለባቸው፡፡
2. መንገድ ለመሻገር የመንገድ መሻገሪያ ዜብራ ምልክቶችን መጠቀም ያስፈሊጋል ፡፡
3. የኤድስ በሽታ በእርግማን የሚመጣ በሽታ ነው፡፡
4. የኤች አይ ቪ ቫይረስ አብሮ በመጫወት ይተላለፋል፡፡
5. የኤች አይ ቪ ቫይረስ ካለባቸው ሰዎች ጋር ስለታማ ነገሮችን በጋራ መጠቀም ችግር የለውም ፡፡

II. ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል ምረጥ/ጪ

6. በኤድስ በሽታ የተያዙ ሰዎች የሚያሳዩት ምልክት የሆነዉ የቱ ነዉ?

ሀ. የሰውነት ሙቀት በተደጋጋሚ መጨመር

ለ. ለረጅም ጊዜ የሚቆይ ሳል

ሐ. የሰውነት ክብደት በፍጥነት መቀነስ

መ. ሁሉም መልስ ነው

7. የኤች አይ ቪ ቫይረስ በቫይረሱ ከተያዘ ሰው በምን ይተላለፋል?

ሀ. መንገድ ላይ አብሮ በመጓዝ

ለ. በደም ንክኪ

ሐ. አብሮ በመጫወት

መ. አብሮ በመማር

8. በትራፊክ አደጋ ምክንያት ሊደርስ የሚችል አደጋ የቱ ነው?

ሀ. የሰዉ ህይወት መጥፋት

ለ. የንብረት መውደም

ሐ. በእንስሳት ላይ የሚደርስ ጉዳት

መ. ሁሉም መልስ ነው፡፡

Biiroo Barnootaa Oromiyaa
ኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ

ኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ 2014/2022

# አካባቢ ሳይንስ

## የተማሪዎች መጽሐፍ

## 3ኛ ክፍል

ዋጋ ________________